**አዋጅ ቁጥር ፲፪/፪ሺ፩**

**የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን ለመመዝገብና ለማስተዳደር የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገመንግሥት የተረጋገጠውን የዜጎች የመደራጀት መብት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁለንተናዊ ዕድገት ውስጥ ያላቸውን ሚና ለመደገፍና ለማሳለጥ የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ቁጥር ፲፪/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር፦

፩. "የበጀት ዓመት" ማለት በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከሐምሌ ፩ እስከ ሰኔ ፴ ወይም በጐርጐሳውያን አቆጣጠር ከጀንዋሪ ፩ እስከ ዲሴምበር ፴፩ ያለው ጊዜ ነው፤

፪. "የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅት" ወይም "የኢትዮጵያ ማህበር" ማለት በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት የተመሰረተ፣ ሁሉም አባላቱ ኢትዮጵያውያን የሆኑ፣ የገቢ ምንጩ ከኢትዮጵያ የሆነና ኢትዮጵያውያን ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠሩት ነው፡፡ ነገር ግን የገቢያቸውን ከ ፲ በመቶ የማይበልጥ ከውጭ ምንጭ የሚገኝ ገቢ የሚጠቀሙ ከሆነ የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሆነው ሊቆጠሩ ይችላሉ፤

**Proclamation No. 12/2009**

**Proclamation for the Registration and Regulation of Charities and Societies**

**WHEREAS,** it is found necessary to enact a law in order to ensure the realization of citizens' right to association enshrined in the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

**WHEREAS,** it is found essential to promulgate a law to aid and facilitate the role of Charities and Societies in the overall development of Ethiopian peoples;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## SECTION ONE
## GENERAL

**1. *Short Title***

This Proclamation may be cited as the "Charities and Societies Proclamation No. 12/2009."

**2. *Definition***

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1. "Budget Year" shall mean the period from Hamle 1 to Sene 30 (E.C) or from 1st January to 31st of December (G.C);
2. "Ethiopian Charities" or "Ethiopian Societies" shall mean those Charities or Societies that are formed under the laws of Ethiopia, all of whose members are Ethiopians, generate income from Ethiopia and wholly controlled by Ethiopians. However, they may be deemed as Ethiopian Charities or Ethiopian Societies if they use not more than ten percent of their funds which is received from foreign sources;

፫. "የኢትጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት" ወይም "የኢትዮጵያ ነዋሪዎች ማህበር" ማለት ሁሉም አባላቱ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ፣ ከ ፲ በመቶ በላይ ከውጭ ምንጭ የሚገኝ ገቢ የሚጠቀም እና በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት የተቋቋመ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ነው፤

፬. "የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት" ማለት በውጭ ሕግ መሰረት የተቋቋመ ወይም የውጭ ዜጎች በአባልነት ያሉበት ወይም ከውጭ ምንጭ የሚገኝ ገቢ የሚጠቀም ወይም የውጭ ዜጎች የሚቆጣጠሩት የበጎ አድራጎት ድርጅት ነው፤

፭."ብዙሃን ማህበራት" ማለት የሙያ ማህበራትን፣ የሴቶች ማህበራትን፣ የወጣት ማህበራትንና ሌሎች ተመሳሳይ የኢትዮጵያ ማህበራትን ያካትታል፤

፮. "ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደምተከተላቸው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፍትሕ ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው፤

፯. "የሥራ መሪ" ማለት ኦዲተርን ሳያካትት የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን የእለት ተእለት አስተዳደር በአጠቃላይ የሚቆጣጠር እና የሚመራ ሰው ነው፤

፰. "ሰው" ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ነው፤

፱. "የሥራ ቦታ" ማለት የአንድ ሰው ሠነዶችና የሂሣብ መዛግብት የሚቀመጡበት ወይም አንድ ሰው ሥራውን የሚያካሂድበት ቦታ ነው፤

፲. "ሕዝባዊ መዋጮ" ማለት በሕዝባዊ ወይም በሥራ ወይም በመኖሪያ ቦታዎች በመሄድ የሚገኘውን ገቢ ለበጎ አድራጎት ተግባሮች እንዲያውለው ገልጾ ገንዘብ ወይም ሌላ ንብረት በዋጋ ወይም በነጻ ለማሰባሰብ የሚደረግ ጥሪ ማለት ሲሆን ለሃይማኖት ወይም ለቀብር አገልግሎት በዋለ መሬት ወይም ሕንፃ ወይም አጠገባቸው ባለ መሬት ላይ የሚደረግ ጥሪን አያጠቃልልም፤

3. “Ethiopian Residents Charities” or “Ethiopian Residents Societies” shall mean those Charities or Societies that are formed under the laws of Ethiopia and which consist of members who reside in Ethiopia and who receive more than 10% of their funds from foreign sources;

4. "Foreign Charities" shall mean those Charities that are formed under the laws of foreign countries or which consist of members who are foreign nationals or are controlled by foreign nationals or receive funds from foreign sources;

5. “Mass-Based Societies” shall include professional associations, women’s associations, youth associations and other similar Ethiopian societies;

6. "Ministry" and “Minister” shall respectively mean the Ministry and Minister of Justice of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

7. "Officer" shall mean a person who has the general control and management of the day to day administration of a Charity or Society and shall not include an auditor;

8. “Person” shall mean any physical or juridical person;

9. "Place of Work" shall mean the place where a person’s records and books of account are kept or the place where a person conducts work;

10. “Public Collection” shall mean an appeal in any public place or by means of visits to places of work or residence; for money or other property whether for consideration or otherwise and which is made in association with a representation that the whole or any part of its proceeds is to be applied for charitable purposes and shall not include appeal made on a land or building used for the purposes of worship or burial or any land adjacent to it;

፲፩. "መተዳደሪያ ደንብ" ማለት የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የተቋቋመባቸዉን ወይም ሊያራምዳቸው የሚችሉ ዓላማዎች ወይም ሀብቱን በሥራ ላይ የሚያውልባቸው መንገዶችን፣ የአባልነት እና የአመራር ቦታዎችን ለማግኘት የሚያበቁ መመዘኛዎችን፣ የአመራር ቦታ በሹመት ወይም በምርጫ የሚሰጥበት መንገድ፤ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የሚተዳደርበት እንዲሁም ከላይ የተዘረዘሩት ጉዳዮች የሚሻሻሉበት መንገድና ሁኔታን ያጠቃልላል፤

፲፪. "የዘርፍ አስተዳዳሪ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፮ የተሰየመ የፌዴራል አስፈጻሚ መሥሪያ ቤት ነው፤

፲፫. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀጽ ፵፯ የተመለከተው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ አባል የሆነ ክልል ነው፤

፲፬. "አስተዳደራዊ ወጪ" ማለት ለደመወዝ፣ ለአበል፣ ለጥቅማ ጥቅም፣ ለዕቃዎችና ለአገልግሎቶች ግዥ፣ ለጉዞ እና ለመስተንግዶ የሚወጡ ለበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ለማህበሩ አስተዳደራዊ ሥራዎች አስፈላጊ የሆነ ወጪ ነው፤

፲፭. "ከውጭ ምንጭ የሚገኝ ገቢ" ማለት ከውጭ አገር የሚደረግ የማንኛውም ዕቃ ወይም ገንዘብ ወይም ዋስትና ስጦታ፣ ክፍያ ወይም ማስተላለፍ ነው፡፡ የውጭ ምንጭ ማንኛውንም የውጭ አገር መንግሥት፣ ኤጀንሲ ወይም ካምፓኒ፤ ዓለም አቀፍ ኤጀንሲ ወይም ማንኛውንም በውጭ አገር ያለ ሰው ያካትታል፤

፲፮. "የሃይማኖት ድርጅት" ማለት የአንድ ሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን ለማደራጀት እና ለማስፋፋት የሚያቋቁሙት ተቋም ሆኖ በዚህ አዋጅ ትርጓሜ የበጎ አድራጎት ዓላማዎች ለማሳካት የተቋቋሙ ድርጅቶችን ወይም የሃይማኖት ድርጅቱ የሚያቋቁማቸው የበጎ አድራጎ ድርጅቶችን አያጠቃልልም፡፡

11. "Rules" shall include the objects for which a Charity or Society is formed, or which it may pursue, or for which its funds may be applied; the qualifications for membership and for the holding of any office; the method of appointment or election to any office; the rules by which the Charity or Society is to be governed; and the method and manner by and in which any of the above matters may be amended;

12. "Sector Administrator" shall mean a Federal Executive Office designated as such in accordance with Article 66 of this Proclamation;

13. "State" shall mean a State specified under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia as a member state of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

14. Administrative costs shall mean those costs incurred for emoluments, allowances, benefits, purchasing goods and services, travelling and entertainments necessary for the administrative activities of a Charity or society;

15. "Income from Foreign source" means a donation or delivery or transfer made from foreign source of any article, currency or security. Foreign sources include the government, agency or company of any foreign country; international agency or any person in a foreign country;

16. "Religious Organization" means an institution established by believers to organize and propagate their religion and shall not include organizations established for the achievement of any charitable purpose as defined in this proclamation or charities established by the religious organizations.

፫ <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

፩. ይህ አዋጅ በሚከተሉት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡-

ሀ. ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች በሚሰሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ወይም የአባላት ጥንቅራቸው ከአንድ ክልል በላይ በሆኑ ማህበራት፤

ለ. በአንድ ክልል ብቻ የሚሠሩ ቢሆንም በውጭ አገር በጎ አድራጎት ድርጅቶች እና በኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት፤

ሐ. በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በሚሰሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት፡፡

፪. ይህ አዋጅ በሚከተሉት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡-

ሀ. በሃይማኖት ድርጅቶች፤

ለ. ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ጋር በሚደረግ ስምምነት መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ በሚንቀሳቀሱ ዓለም አቀፍና የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት፤

ሐ. በዕድር፣ ዕቁብ እና ተመሳሳይ ባህላዊ ወይም ሃይማኖታዊ ይዘት ባላቸው ማሕበራት፤

መ. በሌላ ሕግ በሚሸፈኑ ማህበራት፡፡

3. ***Scope of Application***

1. This proclamation shall be applicable to:

a) Charities or Societies that operate in more than one regional state or Societies whose members are from more than one regional state;

b) Foreign Charities and Ethiopian Resident Charities and Societies even if they operate only in one regional state;

c) Charities or Societies operating in the City Administration of Addis Ababa or Dire-Dawa.

2. This proclamation shall not be applicable to:

a) religious organizations;

b) international or foreign organizations operating in Ethiopia by virtue of an agreement with the Government of The Federal Democratic Republic of Ethiopia;

c) "Edir", "Ekub" and other similar cultural or religious associations;

d) Societies governed by other laws.

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ</u>

፬. <u>መቋቋም</u>

፩. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ "ኤጀንሲ" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

## SECTION TWO
## CHARITIES AND SOCIETIES AGENCY

**4. *Establishment***

1. The Charities and Societies Agency (hereinafter referred to as the "Agency") is hereby established by this Proclamation with its own legal personality and as an institution of the Federal Government.

2. The Agency shall be accountable to the Ministry.

**፭. የኤጀንሲው ዓላማዎች**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት እንዲስፋፉና ተልዕኳቸውን በሕግ መሠረት እንዲወጡ ማስቻልና ማበረታታት፤

፪. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አሠራር ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት ሊሆን የሚችልበትን ሁኔታ መፍጠር፤

፫. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በሕግ መሠረት መስራታቸውን ማረጋገጥ።

**፮. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባራት**

፩. ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ. በዚህ አዋጅ መሠረት ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ፈቃድ መስጠት፣ መመዝገብና መቆጣጠር፤

ለ. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የተሻለ አሠራር እንዲኖራቸው ማረበታታት፤

ሐ. ከሥልጣንና ተግባሩ ጋር ግንኙነት ያላቸውን መረጃዎች ማሰባሰብ፣ መተንተን፣ ማሰራጨት፤

መ. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን ምዝገባ በሚመለከት መረጃ በጋዜጣ ማሳተምና ማሰራጨት፤

ሠ. የመንግሥት አካላት እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የሚሳተፉባቸውን የምክክር መድረኮች ማዘጋጀት፤

ረ. ዓላማውን ለማሳካት የሚያስችል የውሳኔ ሀሳብ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፤

ሰ. ለምዝገባና ፈቃድ ጥያቄ የሚያቀርቡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ጉዳይ ከሚመለከተው ዘርፍ አስተዳዳሪ ጋር በመመካከር መርምሮ መወሰን፤

ሸ. በአዋጅ ቁጥር ፫፻፴፬/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) ስለሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የዘለቄታ በጎ አድራጎት እና የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ሰነዶችን ማረጋገጥና መመዝገብ፤

**5. *Objectives of the Agency***

The Agency shall have the following objectives:

1. to enable and encourage Charities and Societies to develop and achieve their purposes in accordance with the law;
2. to creat a situation in which the operation of Charities and Societies is transparent and accountable;
3. to ensure that Charities and Societies operate legally.

**6. *Powers and Functions of the Agency***

1. The Agency shall have the following powers and functions:

a. to license, register, and supervise Charities and Societies in accordance with this proclamation;

b. to encourage Charities and Societies to have better administration;

c. collect, analyze and disseminate information that has connection with its powers and functions;

d. publish and distribute information about the registration of Charities and Societies in the Gazette;

e. organize consultative fora for governmental organs and Charities and Societies;

f. to make proposals to the Ministry on matters relating to meeting its objectives;

g. take decisions, in cooperation with the concerned Sector Administrator, on the application of Charities and Societies for registration and license;

h. without prejudice to the provisions of Proclamation No. 334/2003 (as amended), to exercise the powers of registration and authentication of documents with regard to Charitable Endowments and Charitable Trusts;

ቀ. ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በመንግሥት በሚጸድቀው ተመን መሠረት የአገልግሎት ክፍያዎችን መሰብሰብ፤

በ. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤

ተ. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በውክልና መስጠት፤ እና

ቸ. ዓላማዎቹን ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን መፈጸም::

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሸ) የተመለከተው ቢኖርም ሚኒስትሩ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽህፈት ቤት በኤጀንሲው ቅጥር ግቢ ቅርንጫፍ እንዲከፍት ወይም ሠራተኞቹን እንዲመድብ ሊያዝ ይችላል::

**፯. <u>የኤጀንሲው አቋም</u>**

ኤጀንሲው:-

፩. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ቦርድ (ከዚህ በኋላ " ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፤

፪. በመንግሥት የሚሾም ዋና ዳይሬክተር፤ እና

፫. አስፈላጊ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል::

**፰. <u>የቦርዱ አባላት</u>**

፩. ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግሥት የሚሰየሙ ሰባት አባላት ይኖሩታል::

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ከሚሰየሙ የቦርድ አባላት መካከል ሁለቱ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ከማህበራት የተውጣጡ ይሆናሉ::

**፱. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩. ከዚህ አዋጅ አፈጻጸም ጋር ተያይዞ የሚነሱ የፖሊሲ ጉዳዮችን መርምሮ የውሳኔ ሃሳብ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

፪. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት አስተዳደርን በተመለከተ ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሔ ይሰጣል፤

i. to collect fees for the services it renders in accordance with the rate to be approved by the Government;

j. to own property, enter into contract, sue and be sued in its own name;

k. to delegate, when it deems necessary, the powers and functions given to it by this Proclamation; and

l. to carry out such other activities necessary for the attainment of its objectives.

2. Notwithstanding Sub-article 1(h) of this Article, the Minister may order the Office of Documents Authentication and Registration to open a branch office in the premises of the Agency or assign its employees.

**7. *Organization of the Agency***

The Agency shall have:

1. A Charities and Societies Board (hereinafter referred to as the "Board");
2. A Director General to be appointed by the Government; and
3. The necessary staff.

**8. *Members of the Board***

1. The Board shall have seven members, including its Chairperson, to be nominated by the government.
2. Among the board members who are appointed in accordance with Sub-article (1) of this Article, two of them shall be nominated from the Charities and Societies.

**9. *Powers and Functions of the Board***

The Board shall have the following powers and functions:

1. deliberates on and makes recommendations to the Minister on policy matters concerning the implementation of this Proclamation;
2. gives solutions to problems that arise in connection with the administration of Charities and Societies;

፫. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በሚሰጠው ውሳኔ ላይ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቀርቡ ይግባኞችን መርምሮ ይወስናል፤

፬. በዚህ አዋጅ መሠረት በኤጀንሲው የሚወጡ መመሪያዎችን መርምሮ ያጸድቃል፤

፭. በዋና ዳይሬክተሩ የሚቀርቡለትን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን የሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች መርምሮ ይወስናል::

## ፲. የቦርዱ ስብሰባ

፩. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል::

፪. በቦርዱ ስብሰባ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል::

፫. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል::

፬. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል::

## ፲፩. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

፩. ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል::

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ:-

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ለኤጀንሲው የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ. የኤጀንሲውን ሠራተኞች የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሰረታዊ ዓላማዎች ተከትሎ በመንግሥት

3. hears appeals from decisions of the Director General in accordance with this Proclamation;
4. approves directives to be issued by the Agency;
5. decides on other matters concerning Charities and Societies submitted to it by the Director General.

## 10. *Meetings of the Board*

1. The Board shall meet once every month. It may; however, conduct emergency sessions as may be deemed necessary.
2. There shall be a quorum where more than half of its members are present.
3. Decisions of the Board shall be made by a majority vote; in case of a tie, however, the Chairperson shall have a casting vote.
4. Without prejudice to the provisions of this Article, the Board may prescribe its own rules of procedure.

## 11. *Powers and Functions of the Director* General

1. The Director General shall be the chief executive of the Agency and shall, according to the general directions given to him by the Ministry, direct and administer the activities of the Agency.
2. Without prejudice to the generalities of Sub-Article (1) of this Article, the Director General shall:
   a. exercise the powers and functions of the Agency specified under Article 6 of this proclamation;
   b. employ and administer the employees of the Agency in accordance with regulations issued by the Government following basic

በሚጸድቅ ደንብ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ. የኤንጀሲውን የሥራ መርሐ ግብርና በጀት ያዘጋጃል፣ በሚኒስቴሩ ሲጸድቅም ሥራ ላይ ያውላል፤

መ. ለኤጀንሲው በተፈቀደው በጀትና የሥራ መርሐ ግብር መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ. ከሦስተኛ ወገኖች ጋር የሚደረጉ ማናቸውንም ግንኙነቶች በተመለከተ ኤጀንሲውን ይወክላል፤

ረ. የኤጀንሲውን የሥራ አፈጻጸምና የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል::

፫. ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኤጀንሲው የሥራ ሃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል::

**፲፪. <u>በጀት</u>**

የኤጀንሲው በጀት በመንግሥት ይመደባል::

**፲፫. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

፩. ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል::

፪. የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብትና ሌሎች ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም በዋናው ኦዲተር በሚሰየም ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ::

principles of Federal Civil Service Laws ;

c. prepare the work programme and budget of the Agency; and implement same upon approval by the Ministry;

d. effect expenditure in accordance with the budget and work programme approved for the Agency;

e. represent the Agency in all its dealings with third parties;

f. prepare and submit to the Ministry the activity and financial reports of the Agency.

3. The Director General may delegate part of the directorial powers and functions to officials and employees of the Agency to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Agency.

**12. *Budget***

The budget of the Agency shall be allocated by the Government.

**13. *Books of Account***

1. The Agency shall keep complete and accurate books of account;
2. The Agency's books of account and any other financial documents shall, every year, be inspected by the General Auditor or by the Auditor who is assigned by the General Auditor.

## ክፍል ሦስት
## የበጎ አድራጎት ድርጅቶች
### ንዑስ ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

**፲፬. ትርጓሜ**

፩. "የበጎ አድራጎት ድርጅት" ማለት ለበጐ አድራጐት ዓላማ ብቻ የተቋቋመና ለህዝብ ጥቅም የሚሰጥ ተቋም ነው።

፪. "የበጎ አድራጎት ዓላማ" የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ. ድህነትን ወይም አደጋን መከላከል፣ መቀነስ ወይም ማስወገድ፤

ለ. የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት እና የአካባቢ ጥበቃን ወይም ማሻሻልን ማፋጠን፤

ሐ. የእንስሳት ደሕንነትን ማስፋፋት፤

መ. ትምህርትን ማስፋፋት፤

ሠ. ጤንነትን ወይም ሕይወት ማዳንን ማራመድ፤

ረ. ጥበብን፣ ባሕልን፣ ቅርስን ወይም ሣይንስን ማዳበር፤

ሰ. አማተር ስፖርትንና የወጣቶችን ደህንነት ማስፋፋት፤

ሸ. በዕድሜ፣ በአካል እና በአዕምሮ ጉዳት፣ በገንዘብ ወይም በሌሎች ምክንያቶች የተቸገሩትን መታደግ፤

ቀ. የአገሪቱን የረጅም ጊዜ የልማት አቅጣጫ መሰረት በማድረግ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማበረታታት፤

በ. የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ተግባራዊነትን ማበረታታት፤

ተ. የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ የጾታ እና የሃይማኖት እኩልነት መረጋገጥን ማበረታታት፤

ቸ. የሕጻናትና የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበርን ማበረታታት፤

ኀ. የግጭት አፈታትን ወይም ዕርቅን ማስፋፋት፤

ነ. የፍትህና የህግ ማስፈጸም አገልግሎቶችን ቀልጣፋነት ማጠናከር፤

## SECTION THREE
## CHARITIES
### Sub-Section One
### General

**14. *Definition***

1. “A Charity” means an institution, which is established exclusively for charitable purposes and gives benefit to the public.
2. “Charitable Purposes” shall include:

a. the prevention or alleviation or relief of poverty or disaster;

b. the advancement of the economy and social development and environmental protection or improvement;

c. the advancement of animal welfare;

d. the advancement of education;

e. the advancement of health or the saving of lives;

f. the advancement of the arts, culture, heritage or science;

g. the advancement of amateur sport and the welfare of the youth;

h. the relief of those in need by reason of age, disability, financial hardship or other disadvantage;

i. the advancement of capacity building on the basis of the country’s long term development directions;

j. the advancement of human and democratic rights;

k. the promotion of equality of nations, nationalities and peoples and that of gender and religion;

l. the promotion of the rights of the disabled and children’s rights;

m. the promotion of conflict resolution or reconciliation;

n. the promotion of the efficiency of the justice and law enforcement services; and

ኘ. ሌሎች ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ የሚደነገጉ ዓላማዎች::

፫. ሕዝባዊ ጥቅም ይኖራል ተብሎ የሚቆጠረው፡-

ሀ. የበጎ አድራጎት ድርጅት ዓላማዎች አንድ ተለይቶ የሚታወቅ ጥቅም ለሕዝቡ የሚያስገኙ ሲሆን፤

ለ. የበጎ አድራጎት ድርጅት ዓላማዎች ሊጠቀሙ የሚገባቸውን ሰዎች የማያገሉ ሲሆን፤ እና

ሐ. ለግለሰቦች ወይም ለድርጅቶች የሚያስገኘው የግል ጥቅም የድርጅቱ ዋና የሥራ ዓላማ በመሆኑ ሳይሆን በአጋጣሚ እና ድርጅቱ ዓላማውን በሚያሳካበት ጊዜ በተቀፅላነት የተገኘ ሲሆን፤

ብቻ ነው::

፬. ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ዓላማዎችንና የህዝብ ጥቅምን በተመለከተ ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል::

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ (በ)፣ (ተ)፣ (ቸ)፣ (ኀ) እና (ነ) በተመለከቱት የበጎ አድራጎት ዓላማዎች ላይ መሰማራት የሚችሉት የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ብቻ ይሆናሉ::

o. any other purposes as may be prescribed by directives of the Agency.

3. A public benefit shall be deemed to exist where:
   a. the purposes of the Charity can generate an identifiable benefit to the public;
   b. the purposes of the Charity do not create a situation wherein its benefits exclude those in need; and
   c. any private benefit of individuals and organizations could be acquired only incidentally and as a secondary consequence of the organization's activities.

4. The Agency may determine the details of charitable purposes and the public benefit by directives.
5. Those who can take part in activities that fall under Sub-article 2 (j), (k), (l), (m) and (n) of this Article shall be only Ethiopian Charities and societies.

## ፲፭. <u>የበጎ አድራጎት ድርጅት ዓይነቶች</u>

፩. የበጎ አድራጎት ድርጅት፡-

ሀ. የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት፤

ለ. የበጎ አድራጎት ተቋም፤

ሐ. የአደራ የበጎ አድራጎት ድርጅት፤ ወይም

መ. የበጎ አድራጎት ማህበር፤

ሆኖ ሊመሰረት ይችላል::

፪. በዚህ ክፍል ንዑስ ክፍል አምስት ስለበጎ አድራጎት ኮሚቴዎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በበጎ አድራጎት ሥራ ለመሠማራት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከቱት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች አንዱን መመሥረትና በቅድሚያ የፈቃድና የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማግኘት ያስፈልጋል::

## 15. *Types of Charities*

1. A Charity may be formed as:
   a. a Charitable Endowment;
   b. a Charitable Institution;
   c. a Charitable Trust; or
   d. a Charitable Society.

2. Without prejudice to the provisions of Sub-section five of this Section concerning Charitable Committees it shall be necessary to form and acquire a Registration and License Certificate in order to carry out charitable acts.

፫. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሥራቸውን የሚያስተባብር የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሕብረት ማቋቋም ይችላሉ:: ዝርዝሩ ጀንሲው በሚያወጣው ዝርዝር መሰረት ይወሰናል::

3. Charities may form a consortium Charity to co-ordinate their activities. Particulars shall be determined by the directives of the Agency.

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቶች

## Sub-Section Two
## Charitable Endowments

### ፲፮. ትርጓሜ

"የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት" ማለት አንድ የተለየ ንብረት በስጦታ ወይም በኑዛዜ ወይም በኤጀንሲው ትዕዛዝ በዘላቂነትና በማይመለስ ሁኔታ ለበጎ አድራጎት ዓላማ ብቻ የሚውልበት ነው::

### 16. *Definition*

A “Charitable Endowment” is an organization by which a certain property is perpetually and irrevocably destined by donation or will or the order of the Agency for a purpose that is solely charitable.

### ፲፯. ለምዝገባ ስለማመልከት

፩. መሥራቹ በሕይወት ያለ ከሆነ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት ምዝገባ የሚጠየቀው በመሥራቹ በራሱ ወይም ለዚህ ጉዳይ በወከለው ሰው ብቻ ነው::

፪. መሥራቹ ከሞተ በኋላ ጥያቄው የሚቀርበው መሥራቹ አደራ በሰጠውና ይህን በተቀበለው ሰው ወይም የመሥራቹን ኑዛዜ በሚያስፈጽሙ ሰዎች ነው::

፫. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተጠቀሱት ሰዎች በማይኖሩበት ጊዜ ንብረትን ለዘለቄታ በጎ አድራጎት ዓላማ የመስጠት ውል ያዘጋጁ፣ ምስክር የሆኑ ወይም ውሉን በአደራ ያስቀመጡ ሰዎች የምዝገባ ጥያቄ ያቀርባሉ::

፬. በዚህ አንቀጽ መሠረት ምዝገባ የመጠየቅ ግዴታ የተጣለባቸው ሰዎች ምዝገባውን ሳይጠይቁ የቀሩ እንደሆነ መሥራቹ ከሞተ ከሦስት ወር በኋላ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ በማንኛውም

### 17. *Application for Registration*

1. The registration of a Charitable Endowment may not be sought during the lifetime of the founder, except by the founder herself/himself or a person designated for that purpose.
2. After the death of the founder, it shall be sought by the person to whom the founder has entrusted such task and who has accepted it or the executors of the founder's will.
3. In default of the persons in Sub-article (1) and (2), it shall be sought by those persons who have drawn up the act of Endowment or who have been witnesses to it or who hold that act in deposit.
4. Where the persons who are bound to seek the registration of the Charitable Endowment fail to do so, the registration of the Charitable Endowment may be sought, three months after the death of its author, by

ይመለከተኛል በሚል ሰው አመልካችነት ወይም በኤጀንሲው አነሳሽነት ሊመዘገብ ይችላል::

፭. ኤጀንሲው የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ከፈለጉ ሊጠቀሙ የሚችሉባቸውን ሞዴል መተዳደርያ ደንቦችን ያዘጋጃል::

**፲፰. ንብረትን ለዘለቄታ በጎ አድራጎት ዓላማ የመስጠት ተግባርን መሻር**

፩. ንብረትን ለዘለቄታ በጎ አድራጎት ዓላማ የመስጠት ተግባር በኤጀንሲው ከመመዝገቡ በፊት መሥራቹ ሊሽረው ይችላል::

፪. የመሥራቹ ወራሾች የመሻር መብታቸውን ሊጠቀሙ የሚችሉት የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ እንዲመዘገብ ለኤጀንሲው ጥያቄ በቀረበ በ፮ ወራት ጊዜ ውስጥ ሳይመዘገብ ከቀረ ነው::

**፲፱. የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቶች አደረጃጀት**

ማናቸውም የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ፣ ሥራ አስኪያጅ፣ ኦዲተርና ሌሎች አስፈላጊ የሥራ ክፍሎች ይኖረዋል::

**፳. የሥራ አመራር ቦርድ ጥንቅር**

፩. የሥራ አመራር ቦርድ አባላት በመሥራቹ ወይም እርሱ በወከለው ሰው ካልተሾሙ ኤጀንሲው የሚሾሙበትን መንገድ ያመቻቻል::

፪. የቦርዱ አባል በማንኛውም ምክንያት ኃላፊነቱን መወጣት ካልቻለ በዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት አዲስ የቦርድ አባል ይሾማል::

፫. የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ቁጥር በምንም ዓይነት ሁኔታ ከሦስት በታች ሊሆን አይችልም::

**፳፩. የሥራ አመራር ቦርዱ ስልጣንና ተግባራት**

የሥራ አመራር ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩. የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ የበላይ

any interested party or by the Agency.

5. The Agency shall draw up model rules for Charitable Endowments that may be of aid to those wishing to use such model.

**18. *Revocation of an Act of Charitable Endowment***

1. The founder of an endowment may revoke it so long as the Charitable Endowment has not been registered by the Agency.
2. The heirs of the founder may only exercise such right of revocation where the Charitable Endowment has not been registered by the Agency within 6 months from an application having been made to Agency with a view to obtaining its registration.

**19. *Structure of Charitable Endowments***

Any Charitable Endowment shall be organized with the structure of Board of Management, Manager, Auditor and other departments as may be necessary.

**20. *Composition of the Board of Management***

1. Where the members of the Board of Management are not appointed by the founder or by aperson designated by the founder the Agency shall facilitate the appointment of such members.
2. Where a member of the Board is, for any reason, unable to perform his duties, a new member shall be appointed according to the rules of the Endowment.
3. The number of members of the Board shall in no case be less than three.

**21. *Powers and Functions of the Board of Management***

The Board of Management shall have the following powers and functions:

አካል ይሆናል፤

፪. የዘለቄታ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን የሚመራ ሥራ አስኪያጅ ይሾማል፣ ያሰናብታል፤ እና

፫. የዘለቄታ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ያስተዳድራል::

**፳፪.የሥራ አመራር ቦርዱ ስብሰባዎች**

፩. የሥራ አመራር ቦርዱ በዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ በተመለከተው መሠረት ይሰበሰባል::

፪. የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ ውሣኔዎችን የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል::

**፳፫. ለቦርዱ አባላት የሚፈፀሙ ክፍያዎች**

፩. በዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ወይም በማናቸውም ሕግ ካልተወሰነ በስተቀር አንድ የቦርድ አባል ምንም ክፍያ አያገኝም::

፪. በቦርድ ስብሰባ ላይ ለመገኘት አንድ አባል ያወጣውን ወጪ ለመሸፈን የሚደረግ የወጪ ማካካሻ እንደ ክፍያ አይቆጠርም::

**፳፬. የሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባራት**

የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት ሥራ አስኪያጅ:-

፩. የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ሥራ ይመራል፣ ድርጅቱን በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ያስተዳድራል፤

፪. ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ድርጅቱን ይወክላል፤

፫. የሥራ አመራር ቦርዱ ውሳኔዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

1. it shall be the supreme organ of the Charitable Endowment;
2. appoint a Manager who shall be responsible to manage the Endowment or dismiss the same; and
3. administer the Endowment as per its rules.

**22.** ***Meetings of the Board of Management***

1. The Board of Management shall meet as prescribed by the rules of the Charitable Endowment.
2. The decisions of the Board of Management shall be taken by majority.

**23.** ***Remuneration of Board Members***

1. A Member of the Board shall not be entitled to remuneration unless a provision about his entitlement to remuneration has been made, by the Charitable Endowment's rules or by any law.
2. Payments made in connection with covering costs incurred by Board Members for the purpose of attending Board meeting shall not be considered as remuneration.

**24.** ***Powers and Functions of the Manager***

The manager of the Endowment shall:

1. direct the work of the Charitable Endowment and administer the Endowment pursuant to its rules;
2. represent the Endowment in all its dealings with the third parties;
3. follow up and supervise the implementation of the decisions of the Board of Management;

፬. የሥራ ዕቅድና በጀት እንዲሁም የሥራና የሂሣብ ሪፖርቶችን ለሥራ አመራር ቦርዱ ያቀርባል፤

፭. የድርጅቱን ገቢ የሚያሳድጉ ሁኔታዎችን ያጠናል፣ በሥራ አመራር ቦርዱ ሲጸድቁ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፮. በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት በድርጅቱ ስም በተከፈቱ የባንክ ሂሣቦች ላይ ይፈርማል፤ እና

፯. ሌሎች በሥራ አመራር ቦርዱ የሚሰጡትን ተያያዥ ተግባራት ያከናውናል፡፡

### ፳፭. <u>የኦዲተር ሥልጣንና ተግባራት</u>

ኦዲተሩ:-

፩. የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱን የገንዘብና የንብረት አስተዳደር ይቆጣጠራል፤

፪. የድርጅቱን የውስጥ ኦዲት ሪፖርት በኢትዮጵያ ተቀባይነትን ባገኘ መመዘኛ መሠረት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤

፫. በዚህ አዋጅ የውጭ ኦዲተርን በተመለከተ የተደነገገው ቢኖርም የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ በማናቸውም ጊዜ የውጭ ኦዲተር ሊጠቀም ይችላል፡፡

### ፳፮. <u>ተጠቃሚዎችን ስለመወሰን</u>

መሥራቹ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ተጠቃሚዎችን በበቂ ሁኔታ ካልወሰነ ቦርዱ ከመሥራቹ ሃሣብ ጋር ይስማማል ብሎ በሚገምተው መልኩ ተጠቃሚዎችን ሊወስን ይችላል፡፡

4. submit work plan and budget as well as reports on the activities and finance of the Endowment to the Board of Management;
5. study conditions that will promote income generating activities of the Endowment and impement such where approved by the Board;
6. Sign on the bank account opened in the name of the Endowment in accordance with its rules; and
7. discharge other related tasks which may be given to him by the Board of Management.

### 25. *Powers and Functions of the Auditor*

The Auditor shall:

1. monitor the financial and proprietary administration of the Charitable Endowment;
2. prepare the internal audit report of the organization in accordance with standards acceptable in Ethiopia;
3. Notwithstanding the provisions of this Proclamation regarding external audits the Charitable Endowment may at any time use an external Auditor.

### 26. *Determining the Beneficiaries*

Where the beneficiaries are not sufficiently determined by the founder, the Board may determine such beneficiaries as it deems consistent with the intention of the founder.

## ንዑስ ክፍል ሦስት
## የበጎ አድራጎት ተቋማት

**፳፯. የበጎ አድራጎት ተቋም**

፩. የበጎ አድራጎት ተቋም ቁጥራቸው ቢያንስ ሶስት በሚደርሱ ሰዎች ለበጎ አድራጎት ተግባራት ብቻ የሚቋቋም የበጎ አድራጎት ድርጅት ነው፡፡

፪. የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅትን አደረጃጀት የሚመለከቱ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ከአስፈላጊ ማስተካከያ ጋር ለበጎ አድራጎት ተቋም አደረጃጀትም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም የተቋሙ መተዳደሪያ ደንብ የበጎ አድራጎት ተቋሙ አደረጃጀት በዚህ አዋጅ ክፍል አራት ስለማህበር አደረጃጀት በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት እንዲመራ ሊደነግግ ይችላል፡፡

**፳፰. የአባላት ሃላፊነቶች እና ግዴታዎች**

፩. እያንዳንዱ የበጎ አድራጎት ተቋም አባል ወይም አዲስ አባል ድርጅቱ እርሱ አባል በነበረበት ጊዜ ወይም አባልነቱ ካበቃ በኋላ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሲፈርስ አባልነቱ ከማብቃቱ በፊት ለነበሩት የድርጅቱ ዕዳዎች እና ሃላፊነቶች እንዲሁም ድርጅቱን ለማፍረስ የሚያስፈልጉ የአገልግሎት ዋጋዎችንና ወጭዎችን ለመሸፈን ከተወሰነ ጣሪያ በላይ ያልሆነ ዋስትና መግባት ይኖርበታል፡፡

፪. ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ተቋማት ለምዝገባ በሚቀርቡበት ወቅት ዋስትና ሊሰጡ የሚገባቸውን አነስተኛ የገንዘብ መጠን በመመሪያ መወሰን ይችላል፡፡

## Sub-Section Three
## Charitable Institutions

**27. *Charitable Institution***

1. A Charitable Institution is a Charity formed by at least three persons exclusively for charitable purposes.
2. The Provisions of this Proclamation relating to the structure of Charitable Endowment shall apply, with the necessary adjustments, to Charitable Institutions.
3. Notwithstanding Sub-article (2) of this Article, the rules of the Institution may; however, provide that the Charitable Institution be structured in the form of a Society as provided for in section four of this proclamation.

**28. *Duties and Responsibilities of Members***

1. Each member of a Charitable Institution and any new member shall undertake to contribute to the assets of the Institution, in the event of its being dissolved while he is a member or within one year after he ceases to be a member, for payment of the debts and liabilities of the Institution contracted before he ceases to be a member and of the charges and expenses of winding up such amount as may be required, not exceeding a specified amount.
2. The Agency may by directives determine the minimum amount of guarantee required for the registration of Charitable Institutions.

፳፱. <u>ለምዝገባ ስለማመልከት</u>

የበጎ አድራጎት ተቋም የማቋቋም ዓላማ ያላቸው ሰዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፰ በተደነገገው መሠረት ለመመዝገብ ለኤጀንሲው ማመልከት አለባቸው::

<u>ንዑስ ክፍል አራት</u>

<u>የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቶች</u>

፴. <u>ትርጓሜ</u>

"የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት" ማለት የአደራ በጎ አድራጐት ድርጅቱን በሚያቋቁመው ሠነድ መሠረት አንድ የተለየ ንብረት ለበጐ አድራጐት ዓላማ ብቻ እንዲውል በአደራ ጠባቂዎች የሚተዳደር ድርጅት ነው::

፴፩. <u>አመሰራረት</u>

፩. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት በስጦታ ወይም በኑዛዜ ወይም በኤጀንሲው ትዕዛዝ ሊቋቋም ይችላል::

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ስጦታ ወይም ኑዛዜ አግባብ ባላቸው የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይመራል::

፫. በስጦታ ወይም ኑዛዜ ውስጥ የሚገኙ በተዘዋዋሪ አመልካች አንቀጾች የአደራ በጎ አድራጐት ድርጅት ለማቋቋም በቂ ይሆናሉ::

፴፪. <u>የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ቀጣይነት</u>

፩. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ለተወሰነ ጊዜ ሊቋቋም ይችላል፤ ሆኖም የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ገቢ ከሚያስገኙ ሥራዎች፣ ከሕዝባዊ መዋጮ ወይም ከማናቸውም ምንጭ ያገኘው ሃብት ድርጅቱ ከተቋቋመበት ዓላማ አይወጣም::

፪. ላልተወሰነ ጊዜ የተቋቋመ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ዘላቂና የማይሻር ይሆናል::

፫. የአደራ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ገቢ ከሚያስገኙ ሥራዎች፣ ከሕዝባዊ መዋጮ ወይም ከማናቸውም ምንጭ ያገኘውን

**29.** ***Application for Registration***

Persons with the intention of forming a Charitable Institution shall apply to the Agency in accordance with Article 68 of this Proclamation.

**Sub-Section Four**
**Charitable Trusts**

**30.** ***Definition***

A “Charitable Trust” is an organization by virtue of which specific property is constituted solely for a charitable purpose to be administered by persons, the trustees, in accordance with the instructions given by the instrument constituting the charitable trust.

**31.** ***Formation***

1. A Charitable Trust may be constituted by a donation or by a will or by order of the Agency.
2. A donation or will under Sub-article (1) of this Article shall be subject to civil law provisions.
3. An implied provision in the donation or will shall suffice for the constitution of the Charitable Trust.

**32.** ***Perpetuity of a Charitable Trust***

1. A Charitable Trust may be constituted for a definite period. However, those assets obtained from income generating activities, public collections or any other sources shall not be used for purposes other than those for which the trust is instituted.
2. Where a Charitable Trust is constituted for an indefinite period, it shall be perpetual and irrevocable.
3. The charitable trust shall keep separate books of account for assets obtained from income generating activities, public

ሃብት በተለየ የሂሳብ መዝገብ መያዝ አለበት፡፡

**፴፫. <u>በአደራ ጠባቂዎቹ የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ</u>**

፩. አደራ ጠባቂዎች የሚሾሙት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ሆኖ እነዚህ አደራ ጠባቂዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፰ በተደነገገው መሠረት የፈቃድና ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ለኤጀንሲው የምዝገባ ጥያቄ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

፪. አደራ ጠባቂዎቹ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት በተቋቋመ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ የምዝገባ ጥያቄ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

፫. አደራ ጠባቂዎቹ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ከማግኘታቸው በፊት በስጦታው ወይም ኑዛዜው ላይ የተመለከተውን ሀብት ባለይዞታነት ወይም ባለቤትነት ወደ አደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ለማስተላለፍ ከሚያስፈልጉ ድርጊቶች በስተቀር ሦስተኛ ወገኖችን የሚያካትት ማናቸውንም ድርጊት መፈፀም አይችሉም፡፡

**፴፬. <u>የአደራ ጠባቂዎች ብዛት</u>**

፩. የአደራ ጠባቂዎች ብዛት በማናቸውም ምክንያት ከ፪ ያነሰ እና ከ፭ የበለጠ ሊሆን አይችልም፡፡ ከ፫ ያነሱ ሰዎች ተጠቅሰው ከሆነ ይህን መመዘኛ ለማሟላት ኤጀንሲው ቀሪዎቹ የሚሾሙበትን መንገድ ያመቻቻል፡፡

፪. ከ፭ በላይ አደራ ጠባቂዎች ተጠቅሰው ከሆነ መሥራት የሚችሉና ፈቃደኝነት ያላቸው በቅድሚያ የተጠቀሱት ፭ ሰዎች ብቻ አደራ ጠባቂ ይሆናሉ፡፡ ቀሪዎቹ ሰዎች ክፍት ቦታዎች ተፈጥረው ካልተሾሙ በስተቀር አደራ ጠባቂ ሊሆኑ አይችሉም፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑት አደራ ጠባቂዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ከሆኑ የአደራ ጠባቂዎች ብዛት ከሦስት በታች እንዲሆን ኤጀንሲው ሊፈቅድ ይችላል፡፡

collections or any other sources.

**33. *Application for Registration by Trustees***

1. Trustees shall be appointed in accordance with Article 35 Sub-article (1) and such trustees shall apply, in the manner provided in Article 68, to the Agency for a certificate of license and registration.

2. The trustees shall apply for the registration of the Charitable Trust within 3 months of constitution of the Charitable Trust.

3. The trustees may not perform any acts involving third parties before acquiring a certificate of registration except those acts necessary for transferring the funds mentioned in the donation or will to the possession or ownership of the Charitable Trust.

**34. *Number of Trustees***

1. The number of trustees shall not in any case be lower than 2 and more than 5. Where less than 3 persons are named ,the Agency shall facilitate the appointment of the number of people required to fulfill this requirement.
2. Where more than 5 persons are named as trustees, the 5 first named and who are able and willing to act shall alone be the trustees, and the other persons named shall not be trustees unless appointed on the occurrence of a vacancy.

3. Notwithstanding sub-article (1) of this Article, the Agency may allow less than 3 persons as trustees where one or more of

፬. በዚህ አንቀጽ መሠረት ከሚሾሙት አደራ ጠባቂዎቹ ቢያንስ አንዱ መደበኛ መኖሪያ ቦታው ኢትዮጵያ ውስጥ መሆን አለበት::

## ፴፭. <u>የአደራ ጠባቂዎች አሿሿም</u>

፩. አደራ ጠባቂውን የሚሾመው የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ያቋቋመው ሰው ወይም እርሱ የወከለው ሰው ነው:: እነዚህ ሰዎች ከሌሉ ኤጀንሲው አደራ ጠባቂው የሚሾምበትን መንገድ ያመቻቻል::

፪. የተሾመው አደራ ጠባቂ ውክልናውን አልቀበልም ካለ ወይም በማናቸውም ምክንያት አደራ ጠባቂነቱን ማከናወን ካልቻለ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት አዲስ አደራ ጠባቂ ይሾማል::

## ፴፮. <u>የበጎ አድራጎት ድርጅትን በአደራ ጠባቂነት መሾም</u>

፩. የአደራ የበጎ አድራጎት ድርጅት የሚያቋቁም ሰው የበጎ አድራጎት ድርጅትን በአደራ ጠባቂነት ከሾመ የተሾመው ድርጅት ስራ መሪዎች የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ያስተዳድራሉ::

፪. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው የበጎ አድራጎት ድርጅት የአደራ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን በኑዛዜው፣ በስጦታው ወይም በኤጀንሲው ትዕዛዝ በተወሰነው መሠረት ከሌሎች ስጦታዎች ወይም ዓላማውን ለማሳካት ከሚጠቀምበት ገቢ ለይቶ በመያዝ ያስተዳድራል::

## ፴፯. <u>የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት አደረጃጀት</u>

፩. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅትን የሚያቋቁም ሰው አደራ ጠባቂ ሥራ አስኪያጅ፣ ገንዘብ ያዥ እና ኦዲተር ካልሾመ ወይም እነዚህኑ የሚሾም ሰው ካልወከለ አደራ ጠባቂዎቹ ከራሣቸው መካከል እነዚህን ይመርጣሉ::

፪. አደራ ጠባቂዎቹ ይህን ምርጫ ያላደረጉ ከሆነ

such trustee is a Charity.

4. At least one of the trustees appointed under this Article shall be an Ethiopian domiciliary.

## 35. *Appointment of Trustees*

1. The trustees may be appointed by the person constituting the Trust, or by the person designated by him. In default of such person the Agency shall facilitate the appointment of such person.
2. Where the trustee so appointed refuses his agency or is for any other reason unable to perform the trusteeship, a new trustee shall be appointed according the rules of the trust.

## 36. *Appointment of a Charity as a Trustee*

1. A person constituting a Charitable Trust may appoint a Charity as a trustee in which case the officers of the Charity will administer the trust.
2. The Charity provided in Sub-article (1) shall administer the trust by the terms of the will, donation or order of the Agency and distinguish it from other donations or income that it utilizes to achieve its purposes.

## 37. *Structure of a Charitable Trust*

1. Where the person constituting the Charitable Trust does not designate a trustee manager, a trustee treasurer and a trustee auditor or does not appoint a person to do the same, the trustees shall among themselves make such designation.
2. The Agency shall make such designation where the trustees fail to make such

ወይም መወሰን ካልቻሉ ኤጀንሲው ይሾማል፡፡

፫. ከሦስት በላይ የሆኑ አደራ ጠባቂዎች ሲኖሩ ያልተሾሙት አደራ ጠባቂዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት የተሾሙት አደራ ጠባቂዎች በተሾሙበት ቦታ ካሉባቸው ሃላፊነቶች ውጭ ሌሎች አደራ ጠባቂዎች ያሏቸው መብቶችና ሃላፊነቶች ይኖሯቸዋል፡፡

፬. አደራ ጠባቂዎቹ ስብሰባቸውን የሚመራ ሊቀመንበር ከመካከላቸው ይመርጣሉ፡፡

designation or are unable to give decision.

3. Where there are more than three trustees those who have not been designated under Sub-article (1) or (2) shall have all the rights and obligations of the other trustees except those rights and obligations inhering in the designated responsibilities.
4. The trustees shall among themselves choose the person who shall serve as the chairperson in the meetings of the trustees.

## ፴፰. <u>የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት አስተዳደር</u>

፩. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት አስተዳደርን በተመለከተ ከአደራ ጠባቂዎቹ ቢያንስ አንዱ በጽሑፍ እስካልተቃወመ ድረስ የአደራ ጠባቂ ሥራ አስኪያጁ የሌሎች አደራ ጠባቂዎች ስምምነት ሳያስፈልገው የማስተዳደር ሥራዎችን ይፈጽማል፡፡

፪. ከማስተዳደር ሥራዎች ውጭ ያሉ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተቃውሞ የቀረበባቸው ውሣኔዎች ከአደራ ጠባቂዎች ውስጥ ቢያንስ ሦስቱ በተገኙበት ስብሰባ በድምጽ ብልጫ ይወሰናሉ፡፡

፫. የተለያዩ ሃሣቦች ከአደራ ጠባቂዎች ውስጥ እኩል ድጋፍ ያላቸው ሲሆኑ የመጨረሻው ውሣኔ የስብሰባው ሊቀመንበር በሚሰጠው ድምጽ ይወሰናል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሰረት በተሰጡ ውሳኔዎች የማይስማሙ አደራ ጠባቂዎች የልዩነት ሃሣባቸው በቃለ ጉባኤው ላይ እንዲመዘገብላቸው መጠየቅ ይችላሉ፡፡

፭. አደራ ጠባቂዎቹ በአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ስራ መሪነታቸው ለፈጸሚቸው ከሥልጣን በላይ ለሆኑ ድርጊቶች በግል ሃላፊ ናቸው፡፡

## 38. *Administration of a Charitable Trust*

1. The trustee manager shall perform all acts of management without the approval of the other trustees except where at least one of the trustees submits a written protest concerning any administrative act.
2. Decisions beyond acts of management and those decisions protested to under Sub-article (1) shall be taken by majority where at least three of the trustees are present.
3. Where opposing notions are supported by an equal number of trustees, the final determination shall lie with the chairperson of the meeting.
4. Those who are against a decision taken under Sub-article (2) and (3) may require that their dissenting opinion be recorded in the minutes.
5. The trustees shall be individually liable for the *ultra vires* acts they take as officers of the charitable trust.

## ፴፱. <u>የአደራ ጠባቂዎች ሥልጣን</u>

፩. አደራ ጠባቂዎቹ በአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ላይ ያላቸው ሥልጣን የአንድ

## 39. *Powers of Trustees*

1. The powers of the trustees on the Charitable Trust are those of an owner.

ባለንብረት ሥልጣን ነው፡፡

፪. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ በተቋቋመበት ሠነድ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር አደራ ጠባቂዎቹ አስቀድመው ለኤጀንሲው ሳያስታዉቁ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን ለሌላ ሰው ሊያስተላለፉ አይችሉም፡፡

፫. አነስተኛ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው አደራ ጠባቂዎች የአደራ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ንብረት ያለ ዋጋ ለሌላ ሊያስተላልፉ አይችሉም፡፡

2. Without prejudice to any provision to the contrary in the act of constitution of the Charitable Trust, the trustees may not alienate immovable property without prior notification to the Agency.

3. Subject to the provisions on small charities the trustees may not alienate the property of a Charitable Trust by a gratuitous title.

## ፵. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅትን ስለመወከል

፩. አደራ ጠባቂ ሥራ አስኪያጁ የአደራ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ይወክላል፡፡ አደራ ጠባቂ ሥራ አስኪያጁ በእርሱ ምትክ ድርጅቱን የሚወክለውን አደራ ጠባቂ ይመርጣል፤ እንዲሁም ማናቸውም የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ጉዳዮች የሚከታተል ጠበቃ መወከል ይችላል፡፡

፪. አደራ ጠባቂዎቹ ከሥልጣን ወሰናቸው ሣያልፉ ለፈጸሟቸው ሕጋዊ ድርጊቶች ተጠያቂ የሚሆነው የአደራ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ነው፡፡

## 40. *Representation of a Charitable Trust*

1. The trustee manager shall represent the Charitable Trust. The trustee manager shall nominate the trustee who shall act in his stead and may also appoint an advocate to represent the Charitable Trust in any proceedings.
2. The Charitable Trust shall be liable for juridical acts done by the trustees within their powers.

## ፵፩. ለአደራ ጠባቂዎች የሚፈፀም ክፍያ

፩. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ በተቋቋመበት ሠነድ ወይም በማናቸውም ሌላ ሕግ ክፍያን የተመለከቱ ድንጋጌዎች ከሌለ በቀር አደራ ጠባቂ ክፍያ የማግኘት መብት አይኖረውም፡፡

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም ሁሉም አደራ ጠባቂዎች ክፍያ ሊፈጸም እንደሚገባ በጽሁፍ ሲስማሙ እና ኤጀንሲው ሲያፀድቅ በባለሙያነት የሠራ አንድ አደራ ጠባቂ ለአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ለሰጠው ወይም የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን በመወከል ለፈጸማቸው ድርጊቶች ከበጎ አድራጎት ድርጅቱ ሀብት ተመጣጣኝ ክፍያ ያገኛል፡፡

፫. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም

## 41. *Remuneration of Trustees*

1. A trustee shall not be entitled to remuneration unless a provision about his entitlement to remuneration has been made, by the trust instrument or by any law.
2. Notwithstanding Sub-article (1) of this Article, a trustee who acts in a professional capacity shall be entitled to receive reasonable remuneration out of the trust funds for any services that he provides to or on behalf of the trust if all the trustees have agreed in writing and approved by the Agency that he may be remunerated for the services.
3. Notwithstanding sub-article (1) of this

አንድ አደራ ጠባቂ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ከማስተዳደር ጋር በተያያዘ በግሉ ያወጣቸው ወጭ እና ሃላፊነቶች እንዲተኩለት የመጠየቅ መብት አለው፡፡

**፵፪. <u>የአደራ ጠባቂዎች ኃላፊነት</u>**

አደራ ጠባቂዎች በውክልና ድንጋጌዎች መሠረት ለአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ተጠቃሚዎችና እንደ ነገሩ ሁኔታ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ሲቀር ንብረቱን መቀበል ለሚገባቸው ሰዎች የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን መልካም አስተዳደር በሚመለከት ሃላፊ ይሆናሉ፡፡

**፵፫. <u>የአደራ ጠባቂው ሥራ መልቀቅ</u>**

፩. የአደራ ጠባቂው ሥራ የመልቀቅ ሃሣብ ካለው ስራውን ከመልቀቁ ከሁለት ወር በፊት ለሌሎች አደራ ጠባቂዎች እና ለኤጀንሲው ሳያስታውቅ ቢቀር ከዚህ የተነሣ በአደራ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ላይ ለሚደርሰው ኪሣራ ኃላፊ ይሆናል፡፡

፪. አደራ ጠባቂው ሥልጣኑን ለሌላ አደራ ጠባቂ እስከሚያስተላልፍ ድረስ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን የማስተዳደር ኃላፊነት አለበት፡፡

፫. አንድ አደራ ጠባቂ የሥራ መልቀቂያ ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ከማለፉ ፩ ወር አስቀድሞ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ባቋቋመው ሰው ወይም ይህን ለመፈጸም ሥልጣን በተሰጠው ሰው፤ እነዚህ ባይኖሩ በኤጀንሲው አዲስ አደራ ጠባቂ ይሾማል፡፡

**፵፬. <u>የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ማስያዝ</u>**

፩. የተጠቃሚዎች አበዳሪ የሆኑ ሰዎች የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማናቸውንም ተጠቃሚው ሊያገኝ የሚገባውን አበል በማናቸውም ሁኔታ ማስያዝ አይችሉም፡፡

፪. ለተወሰነ ጊዜ የተቋቋመ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ሲፈርስ ንብረቱን

Article a trustee is entitled to indemnity for all personal expenses and obligations arising out of the administration of the Charitable Trust.

**42.** ***Liability of Trustees***

The trustees shall be liable for the good management of the Charitable Trust, in accordance with the provisions relating to agency, to the beneficiaries of the Charitable Trust and where applicable to the persons who are to receive the property at the termination of the Charitable Trust.

**43.** ***Resignation of a Trustee***

1. A trustee shall be liable for any consequent loss to the Charitable Trust where he does not notify the other trustees and the Agency of his intention to resign two months prior to his resignation.
2. A trustee shall remain liable for the administration of the charitable trust until he hands over the trusteeship.
3. Where a trustee applies for resignation, a new trustee shall be appointed by the person constituting the trust, by the person on whom such power has been conferred, or in default of any such person, by the Agency 1 month prior to the expiry of the notice prescribed in sub-article (1).

**44.** ***Attaching Charitable Trusts***

1. The creditors of beneficiaries may in no case attach a Charitable Trust or any allowance to which a beneficiary is entitled.
2. The creditors of persons who are to receive the property forming the object of the Charitable Trust constituted for a definite

ለመውሰድ መብት ያላቸው ሰዎች አበዳሪዎች የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ማስያዝ ወይም የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ በሚቀርበት ጊዜ ባለዕዳውን መተካት ይችላሉ::

፫. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ቢኖርም በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፴፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ከገቢ ማስገኛ ሥራዎች፣ ከሕዝባዊ መዋጮ ወይም ከማናቸውም ምንጭ በተገኙ ንብረቶች ላይ አበዳሪዎች መብት አይኖራቸውም::

፵፭. <u>የተጠቃሚዎች መብቶች</u>

፩. ተጠቃሚዎች በአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ማቋቋሚያ ሠነድ መሠረት የሚገባቸው ጥቅም እንዲሰጣቸው የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ሊጠይቁ ይችላሉ::

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠቃሚዎቹ መብቶቻቸውን የሚጎዳ ሁኔታ ሲፈጠር አደራ ጠባቂው እንዲሻር ወይም ተገቢ የሆነ ዋስትና እንዲሰጥ ኤጀንሲውን መጠየቅ ይችላሉ::

፫. ተጠቃሚዎቹ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ አካል በሆኑ ንብረቶች ላይ የማዘዝ ወይም የማስተዳደር አንዳች መብት የላቸውም::

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው ቢኖርም እነዚህን ንብረቶች በሚመለከት የይርጋ ዘመን እንዲቋረጥ ማድረግን በመሳሰለው ሥራ መብቶቻቸውን የመጠበቅ ሥራዎችን ብቻ መፈጸም ይችላሉ::

፭. ተጠቃሚዎች ሦስተኛ ወገኖች እንዲያውቁት አንድን ንብረት የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ንብረት አካል መሆኑን በማስታወቂያ መግለጽ ይችላሉ::

፮. መሥራቹ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ተጠቃሚዎችን በበቂ ሁኔታ ካልወሰነ አደራ ጠባቂዎቹ ከመሥራቹ ሃሣብ ጋር ይስማማል ብለው በሚገምቱት መልኩ ተጠቃሚዎችን ሊወስኑ ይችላሉ::

period may at the dissolution of the Charitable Trust attach such property, or may replace the debtor at the time of termination.

3. Notwithstanding Sub-article (2) of this Article, the creditors shall not have rights on those assets obtained from income generetaing activities, public collections or any other sources under subarticle (1) of Article 32(1) of this Proclamation.

**45.** ***Rights of Beneficiaries***

1. The beneficiaries may claim from the Charitable Trust the making over of the interest, which, according to the act of constitution of the Charitable Trust, is to accrue in their favor.
2. Without prejudice to the provisions of Sub-article (1) of this Article where the rights of beneficiaries are jeopardized, they may apply to the Agency for the dismissal of the trustee or to compel him to give appropriate guarantees.
3. The beneficiaries of the Charitable Trust have no right to dispose of or to administer the property forming the object of the Charitable Trust.
4. Notwithstanding the provision of Sub-article (3), they may only do those acts which preserve their rights, such as the interruption of a prescription in relation to such property.
5. The beneficiaries may make publications with a view to informing third parties of the fact that certain property forms the object of the Charitable Trust.
6. Where the beneficiaries are not sufficiently determined by the founder, the trustees may determine such beneficiaries as they deem consistent with the intention of the founder.

## ንዑስ ክፍል አምስት

## የበጎ አድራጎት ማህበራት እና የበጎ አድራጎት ኮሚቴዎች

**፵፮. ትርጓሜ**

፩. "የበጎ አድራጎት ማህበር" ማለት ለበጎ አድራጎት ዓላማ የተቋቋመ ማህበር ነው፤

፪. "የበጎ አድራጎት ኮሚቴ" ማለት ቁጥራቸው ፭ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ከሕዝብ ገንዘብ ወይም ሌላ ንብረት ለበጎ አድራጎት ዓላማ ለመሰብሰብ ሃሣብ ያላቸው የተፈጥሮ ሰዎች ስብስብ ነው።

**፵፯. የበጎ አድራጎት ማህበር**

፩. አግባብነት ያላቸው የማህበር አደረጃጀትንና አሰራርን የሚመለከቱ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ለበጎ አድራጎት ማህበራት ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ ስለ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የተቀመጡት አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ለበጎ አድራጎት ማህበራት ተፈፃሚ ይሆናሉ።

**፵፰. የበጎ አድራጎት ኮሚቴዎችን ስለ ማጽደቅ**

፩. የበጎ አድራጎት ኮሚቴዎች በኤጀንሲው ሳያፀድቁ ገንዘብ ወይም ንብረት ማሰባሰብ ወይም ማናቸውንም ድርጊት መፈጸም አይችሉም።

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ኮሚቴውን ለማቋቋም በሚደረጉ አስፈላጊ እንቅስቃሴዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

፫. ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ኮሚቴዎችን ሲያጸድቅ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፷፱ እና ፸ ድንጋጌዎች በማገናዘብ መወሰን አለበት።

**፵፱. የሂሣብ መግለጫ**

፩. የበጎ አድራጎት ኮሚቴው ተቀባይነት ባላቸው መመዘኛዎች መሰረት ዓመታዊ የሂሣብ መግለጫውን ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት።

፪. የበጎ አድራጎት ኰሚቴው የተቋቋመው ከአንድ ዓመት ላነሰ ጊዜ ከሆነ ይህ ጊዜ

## Sub-Section Five

## Charitable Societies and Charity Committees

**46. *Definition***

1. A "Charitable Society" shall mean a Society which is established for charitable purposes.
2. A "Charity Committee" is a collection of five or more natural persons who have come together with the intent of soliciting money or other property from the public for purposes that are charitable.

**47. *Charitable Society***

1. All appropriate Provisions of this Proclamation concerning the structure and working of Societies shall apply to Charitable Societies.
2. Without prejudice to the provisions of Sub-article (1) of this Article all appropriate provisions of this proclamation concerning Charities shall apply to Charitable Societies.

**48. *Approval of Charity Committees***

1. Charities Committees may not collect funds or perform any other activities without acquiring an approval from the Agency.
2. Sub-article (1) of this Article shall not apply to activities necessary for the formation of a Charity Committee.
3. The Agency shall consider Articles 69 and 70 of this proclamation when approving a Charity Committee;

**49. *Statement of Accounts***

1. A Charity Committee shall submit its annual statement of accounts that conform to acceptable standards to the Agency.
2. A Charity Committee should submit its statement of accounts at its dissolution where the length of time for which the

እንዳለቀ የሂሣብ መግለጫ ማቅረብ አለበት፡፡

**፶. የበጎ አድራጎት ኮሚቴ አደረጃጀት**

፩. የበጎ አድራጎት ኮሚቴን የማፅደቅ ውሣኔ መስራች አባላት እና የበጎ አድራጎት ኮሚቴውን ኘሬዚዳንት፣ ገንዘብ ያዥና ኦዲተር ዝርዝር ሁኔታ ማሳየት ይኖርበታል፡፡

፪. ውሣኔው የበጎ አድራጎት ኮሚቴውን ዓላማዎች እና ዓላማዎቹን የሚያሳካበትን ጊዜ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

፫. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ውሣኔው የበጎ አድራጎት ኮሚቴው ሥራዎች እንዴት መከናወን እንዳለባቸው መወሰን እና በኮሚቴው የሚሰበሰበውን ገንዘብ እና ንብረት መጠንና አጠቃቀሙን ለመቆጣጠር አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

**፶፩. የአባላት ሃላፊነት**

፩. ከበጎ አድራጎት ኮሚቴው እንቅስቃሴ ለሚመነጩ ግዴታዎችና ዕዳዎች አባላት ወይም የስራ መሪዎች በአንድነትና በነጠላ ሃላፊ ይሆናሉ፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገውን በተመለከተ ማናቸውም ለጋሽ፣ አባል፣ ተጠቃሚ፣ ኤጀንሲው ወይም የዘርፍ አስተዳዳሪ ክስ የማቅረብ መብት አለው፡፡

**፶፪. በቂ ያልሆነ ገንዘብና ንብረት**

፩. በበጎ አድራጎት ኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብና ንብረት በኮሚቴው የተሰበሰበውን ዓላማ ለማሣካት በቂ ካልሆነ ወይም ዓላማውን ማሳካት የማይቻል ከሆነ ይህ ገንዘብ ወይም ንብረት የኮሚቴው መቋቋም በፀደቀበት ውሣኔ መሠረት በሥራ ላይ ይውላል፡፡

፪. በውሳኔው ውስጥ ይህን በሚመለከት የተገለፀ ነገር የሌለ እንደሆነ ገንዘቡ ወይም ንብረቱ በኤጀንሲው ቁጥጥር ሥር ሆኖ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት

Charity Committee is formed is not longer than one year.

**50.** ***Structure of a Charity Committee***

1. The decision granting the approval of the Charity Committee shall specify the particulars of persons who constitute the Charity Committee and those who shall act as president, treasurer and auditor of the Charity Committee.
2. The decision shall specify the purposes of the Charity Committee and the time within which it has to achieve them.
3. The decision shall determine, where appropriate, the manner in which the activities of the Charity Committee may be carried out and prescribe such measures as are necessary to control the amount and the use of the funds collected by the Charity Committee. Particulars shall be determined by directives.

**51.** ***Liability of Members***

1. The members or officers of a Charity Committee shall be jointly and severally liable for obligations and debts arising out of its activities.
2. Any donor, member, beneficiary, the Agency or the Sector Administrator shall have standing for the purpose of Sub-article 1.

**52.** ***Insufficient Fund and Property***

1. Where the money or property collected by the Charity Committee is insufficient to attain the object which the Charity Committee proposed to achieve, or where achievement of its purpose becomes impossible, such money or property shall have the destination prescribed by the decision which has approved the Charity Committee.
2. In default of Provision to that effect the money or property shall be placed at the disposal of the Agency and shall be destined for a similar charitable purpose in

ለተመሣሣይ የበጎ አድራጎት ዓላማ ይውላል፡፡

፫. ለበጎ አድራጎት ኮሚቴው ገንዘቡን ወይም ንብረቱን የሰጡ ሰዎች መልሰው ሊወስዱት አይችሉም፡፡

### ፶፫. ቀሪ ገንዘብና ንብረት

፩. በበጎ አድራጎት ኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብ ወይም ንብረት ዓላማውን ለማሣካት አስፈላጊ ከሆነው በላይ ከሆነ ቀሪው ገንዘብ ወይም ንብረት ኮሚቴውን ባፀደቀው የኤጀንሲው ውሣኔ መሠረት ሥራ ላይ ይውላል፡፡

፪. በውሳኔው ውስጥ ይህን በሚመለከት የተገለፀ ነገር የሌለ እንደሆነ ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ኤጀንሲው የሚያዝበት ሆኖ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ለተመሣሣይ የበጎ አድራጐት ዓላማ ይውላል፡፡

፫. ለበጎ አድራጎት ኮሚቴው ገንዘቡን ወይም ንብረቱን የሰጡ ሰዎች መልሰው ሊወስዱት አይችሉም፡፡

### ፶፬. ወደ ዘላቂ በጎ አድራጎት ድርጅትነት ስለመለወጥ

፩. የበጎ አድራጎት ኮሚቴው በፀደቀበት ውሣኔ ላይ በተመለከተው መሠረት በኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብ ወይም ንብረት ለአንድ ለተወሰነ ዘላቂ ዓላማ የሚውል ከሆነ ይህንኑ ዓላማ ለማሣካት ዘላቂ የበጎ አድራጎት ድርጅት ይቋቋማል፡፡

፪. በበጎ አድራጎት ኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብ ወይም ንብረት የታቀደውን ዓላማ ለማሳካት አስፈላጊ ከሆነው እጅግ የበዛ ከሆነ የኮሚቴው አባላት በዘላቂ የበጎ አድራጎት ድርጅትነት ለመመዝገብ ፈቃድ እንዲሰጣቸው ኤጀንሲውን ሲጠይቁና ሲፈቀድላቸው ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡

## ክፍል አራት
## ማህበራት

### ፶፭. ትርጓሜ

፩. "ማህበር" ማለት ዓላማው ትርፍ ለማግኘት ያልሆነ የአባላቱን መብትና ጥቅም

accordance with the Provisions of this Proclamation.

3. Persons who have donated money or property to the Charity Committee may not claim it back.

### 53. *Balance*

1. Where the money or property collected by the Charity Committee amounts to more than what is necessary for the attainment of the proposed purpose, the balance shall have the destination prescribed by the decision of the Agency approving the Charity Committee.
2. In the absence of any Provision to that effect, it shall be placed at the disposal of the Agency and shall be destined for a similar charitable purpose in accordance with the Provisions of this Proclamation.
3. Persons who have given money or property to the Charity Committee may not take it back.

### 54. *Change into a Charitable Endowment*

1. Where under the decision approving the Charity Committee the money or property collected by the Charity Committee is to be destined to a specific lasting object, a Charitable Endowment shall be constituted for the attainment of such object;
2. Where the money or property collected by the Charity Committee is significantly larger than what is necessary for the attainment of the proposed purpose, the members of a Charity Committee may seek permission and apply to the Agency for registration as a Charitable Endowment.

## SECTION FOUR
## SOCIETIES

### 55. *Definition*

1. "Society" means an association of persons organized on non-profit making and

ለማስጠበቅ እና ተመሳሳይ ሕጋዊ ዓላማዎችን ለማከናወን እንዲሁም ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ተቋማት ጋር ለመተባበር በአባላቱ ስምምነት የተመሠረተ የሰዎች ስብስብ ነው፡፡

፪. ማህበራት ሥራዎቻቸውን የሚያስተባብር የማህበራት ሕብረት ማቋቋም ይችላሉ:: ዝርዝሩ ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል::

voluntary basis for the promotion of the rights and interests of its members and to undertake other similar lawful purposes as well as to coordinate with institutions of similar objectives.

2. Societies may form a consortium Society to coordinate their activities. Particulars shall be determined by the directives of the Agency.

## ፶፮. የማህበራት ሕጋዊ ሰውነት

፩. ማህበራት በኤጀንሲው እንደተመዘገቡ ሕጋዊ ሰውነት ያገኛሉ::

፪. የማህበር አባልነት ለሶስተኛ ወገኖች ተላልፎ አይሰጥም ወይም አይተላለፍም::

## 56. *Legal Personality of Societies*

1. Societies shall acquire legal personality upon registration by the Agency.
2. Membership in a Society shall not be transferred or passed to third parties.

## ፶፯. የማህበራት መብቶችና ግዴታዎች

፩. ማንኛውም ማህበር የማህበሩን መስፈርት ለሚያሟላ አዲስ አባል ክፍት መሆን አለበት::

፪. ማንኛውም ማህበር የሚመራው በአባላት ሙሉ ተሳትፎ በተመረጡ ሰዎች ነው::

፫. ማንኛውም የማህበር አባል አንድና እኩል ድምጽ አለው::

፬. ማንኛውም ማህበር በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ካልሆነ በቀር አባላትን ሊቀበልና ሊያሰናብት አይችልም::

፭. አባልነቱ እንዲቋረጥ የሚደረግ ማንኛውም የማህበር አባል የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በሥራ አስፈጻሚው የመሰማት መብት አለው::

፮. ማህበሩ የፌዴራል ባህሪ እና ስያሜ ያለው ከሆነ የሥራው ቦታ ወይም የአባላት ጥንቅር ቢያንስ የአምስት ክልሎች ውክልና ያለው መሆን አለበት::

፯. ኢትዮጵያውያን ብዙሃን ማህበራት በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና በምርጫ ሂደት በተለይም ትምህርታዊ ሴሚናሮችን በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በማዘጋጀት፣ የተወዳዳሪዎችን ፕሮግራም በመረዳት፣

## 57. *Rights and Obligations of Societies*

1. Any Society shall be open to a new member that fulfills the requirements of the Society.
2. Any Society shall be managed by persons elected through the full participation of members.
3. Every member of any Society shall have equal and one vote.
4. No Society may admit or dismiss members except as provided by its rules.
5. The member of any Society whose membership is terminated shall have the right to be heard by the executive organ before a final decision is made.
6. Where the Society has Federal character and nomenclature, its work place and composition of the members shall show the representation of at least five Regional States.
7. Ethiopian mass-based organizations may actively participate in the process of strengthening democratization and election, particularly in the process of conducting educational seminars on current affairs,

የምርጫ ሂደቶችን በመታዘብና ከምርጫ አስፈጻሚ አካላት ጋር በመተባበር ረገድ በንቃት መሳተፍ ይችላሉ::

፰. የማንኛውም ማህበር መተዳደሪያ ደንብ በአባላቱ አብላጫ ድምጽ የሚሻሻል መሆን አለበት::

፱. ማንኛውም ማህበር አባላቱ በጠየቁ ጊዜ ስለማህበሩ እንቅስቃሴ የሚገልፁ ሰነዶችን የማሳየት ግዴታ አለበት::

**፶፰. <u>የማህበራት አደረጃጀት</u>**

፩. የማንኛውም ማህበር አደረጃጀት በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል::

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም ማንኛውም ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ፣ አስፈላጊ የሥራ መሪዎች እና የውስጥ ኦዲተር የያዘ መሆን አለበት::

፫. የውስጥ ኦዲተሩ በማህበሩ የስራ መሪነት ቦታ ሊይዝ አይችልም::

**፶፱. <u>የጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባራት</u>**

ጠቅላላ ጉባኤው የማህበሩ የበላይና የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ ሆኖ:-

፩. የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፣ ያሻሽላል፤

፪. የማህበሩን የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ይመርጣል፣ ያግዳል፣ ያሰናብታል፤

፫. በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የማህበሩን ኦዲተር ይመርጣል፣ ያግዳል፣ ያሰናብታል፤ ክፍያውን ይወስናል፤

፬. በማህበሩ የፖሊሲና ስትራቴጂ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፤

፭. በማህበሩ ሌሎች አካላት ሥልጣንና ተግባራት ስር በማይወድቁ ማህበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፤

፮. የማህበሩን መፍረስ ይወስናል፤

፯. በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የተሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል::

understanding the platforms of candidates, observing the electoral process and cooperating with electoral organs.

8. The rules of any Society shall be subject to amendment by the vote of a majority of members.
9. Any Society shall, upon its member's request, disclose documents that show its activities.

**58. *Structure of Societies***

1. The organizational structure of any Society shall be determined by its rules.
2. Notwithstanding Sub-article (1) of this Article, no Society shall be organized without having a General Assembly, the necessary Officers and an Internal Auditor.
3. An Internal Auditor shall not assume the position of an Officer.

**59. *Powers and Functions of the General Assembly***

The General Assembly of the Society being the supreme and final decision making organ shall:

1. enact and amend the rules of the Society;
2. appoint, suspend or dismiss the executive committee of the Society;
3. appoint, suspend or dismiss the Auditor of the Society and decide on his remuneration based on its rules;
4. decide on policy and strategy matters of the Society;
5. decide on all matters concerning the society which do not fall within the powers and functions of other organs of the society;
6. decide on dissolution of the Society;
7. perform other functions entrusted to it by the rules of the Society.

**፷. <u>ከጠቅላላ ጉባኤው ውሣኔዎች መለየት</u>**

፩. የተለየ ሃሳብ ያለው የማህበር አባል የልዩነት ሃሳቡን በቃለ-ጉባኤው ላይ ለይቶ ማስፈር ይችላል፡፡

፪. ማንኛውም የማህበር አባል በጠቅላላ ጉባኤው የተላለፈው ውሣኔ የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጎች ይጥሳል ብሎ ሲያምን ለኤጀንሲው ሊያመለክት ይችላል፡፡

**60. *Dissents from the Resolutions of the General Assembly***

1. Any member of the Society who has dissenting opinion may record his opinion separately in the minutes.
2. Any member of the Society may apply to the Agency where he believes that the decisions rendered by the General Assembly contravene the rules of the Society or other relevant laws.

**፷፩. <u>የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባዎች</u>**

፩. የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎች በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በተደነገገው መሠረት ይካሄዳሉ፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ መደበኛ ስብሰባ በ፴ ቀናት ውስጥ ያልተጠራ ከሆነ ኤጀንሲው በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አባላት ጠያቂነት በሰብሳቢው አማካይነት ወይም በራሱ የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

፫. የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ የተጠራው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ከሆነ ኤጀንሲው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ የሚሆን ሰው ለምርጫ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፬. የማህበሩ ምልዐተ ጉባኤ በመተዳደሪያ ደንቡ በተወሰነው መሠረት ይሆናል፡፡ ይህን የሚመለከት ድንጋጌ በሌለበት ሁኔታ የስብሰባው አብዛኛው አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይኖራል፡፡ ለሁለት ተከታታይ ስብሰባዎች ምልዓተ-ጉባዔ ካልተሟላ በሚቀጥለው ሦስተኛ ስብሰባ ከአባላቱ ሃምሳ በመቶ ባይገኙም በኤጀንሲው ውሳኔ ምልዓት ጉባዔ እንደተሟላ

**61. *Meetings of the General Assembly***

1. The meetings of the General Assembly shall be held as is provided for in the rules of the Society.
2. Where the Chairperson of the Assembly fails to convene the regular meeting of the General Assembly within 30 days in accordance with Sub-article (1) of this Article, the Agency may, upon request of one or more members or officers of the Society convene the meeting of the General Assembly through the Chairperson or by its own.
3. Where the meeting of the General Assembly was convened in accordance with Sub-article (2) of this Article, the Agency may, where appropriate, nominate a Chairperson of the General Assembly.
4. A quorum of the Society shall be as is provided for in its rules. Failing such provision, a simple majority of the Assembly shall constitute a quorum. Where the quorum is not fulfilled for two consecutive meetings, the quorum shall be deemed to have been fulfilled on the third, such meeting despite there not being a fifty percent presence upon the decision of the

ይቆጠራል፡፡

፭. የጠቅላላ ጉባኤው ውሣኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ድምጽ እኩል ሲሆን ሰብሳቢው ወሣኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡ የማህበሩ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት በማናቸውም ጊዜ ቢሆን የዲሞክራሲ መርሆችን የተመረኮዘ መሆን አለበት፡፡

፮. በጠቅላላ ጉባኤው አጀንዳ ላይ ያልሰፈሩ ጉዳዮችን በተመለከተ የተሰጡ ውሣኔዎች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

## ፷፪. የኦዲተር ሥልጣንና ተግባራት

ኦዲተሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት አለው፤

፩. የማህበሩን ገንዘብና ንብረት አስተዳደር ይቆጣጠራል፡፡

፪. በኢትዮጵያ ተቀባይነት ባገኙ መመዘኛዎች መሠረት የማህበሩን የውስጥ ኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡

፫. በዚህ አዋጅ ስለ ውጭ ኦዲት የተደነገጉት ቢኖሩም ማህበሩ በማንኛውም ጊዜ በውጪ ኦዲተር ሊጠቀም ይችላል፡፡

## ፷፫. አባላትን የሚመለከቱ መረጃዎች

፩. የማህበሩ የሥራ መሪዎች የአባላቱን ዝርዝር ጉዳዮች ይመዘግባሉ፣ ይጠብቃሉ፣ ሲጠየቁ ለኤጀንሲው ያቀርባሉ፡፡

፪. ከማህበራት የሚፈለጉ መረጃዎች ዝርዝር ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

Agency.

5. Decisions of the General Assembly shall be taken by the majority. In case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote. The meetings procedures of the Society shall at all times conform to democratic principles.
6. A decision not relating to the items on the agenda of the General Assembly shall be of no effect.

## 62. *Powers and Functions of the Auditor*

The Auditor shall have the following powers and functions:

1. monitor the financial and property administration of the Society;
2. prepare the internal audit report of the Society in accordance with standards acceptable in Ethiopia and submit to the General Assembly;
3. Notwithstanding the Provisions of this Proclamation regarding external audits the Society may at any time use an external auditor.

## 63. *Information about Members*

1. The Officers of the Society shall record and keep the particulars of its members and furnish the same to the Agency upon request;
2. The particular information required from Societies shall be determined by the directives of the Agency.

## ክፍል አምስት

## የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አመሰራረት፣ ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ

### ንዑስ ክፍል አንድ

### የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አመሰራረት

**፷፬. አመሰራረት**

፩. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጡ ደንቦች የተቀመጡ መስፈርቶችን አሟልተው ሲገኙ እንደተመሰረቱ ይቆጠራል፡፡

፪. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በተመሠረተ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ለምዝገባ ማመልከት አለበት፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በቂ ምክንያት መኖሩን ካሳየ የጊዜ ገደብ ቢያልፍም ለምዝገባ እንዲያመለክት ኤጀንሲው ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**፷፭. የመመስረት ውጤት**

፩. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት በመመስረታቸው ብቻ ሕጋዊ ሰውነት አይኖራቸውም፡፡

፪. የተመሰረተው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሲመዘገብና ሕጋዊ ሰውነት ሲያገኝ መብቶቹና ግዴታዎቹ ወደ ተመዘገበው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ይተላለፋሉ፡፡

፫. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ከመመዝገቡ በፊት የሚያሰባስበው ገንዘብ ወይም ንብረት ከብር ፶፼ (ሃምሳ ሺህ ብር) በላይ ሊሆን አይችልም፡፡

፬. በሕግ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ያልተመዘገበ የተመሠረተ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር እንዲቋረጥ ምክንያት ይሆናል፡፡

## SECTION FIVE

## FORMATION, LICENSING AND REGISTRATION OF CHARITIES AND SOCIETIES

### Sub-Section One

### Formation of Charities And Societies

**64.** ***Formation***

1. Charities and Societies shall be deemed to be formed when they fulfill the minimum requirements set forth in this Proclamation and regulations issued to implement this Proclamation.
2. Any Charity or Society shall apply for registration within three month of its formation.
3. Irrespective of the provision of Sub-article (2) of this Article, the Agency may allow a Charity or Society to apply for registration notwithstanding that the time limit has passed where good cause has been shown.

**65.** ***Effects of Formation***

1. Merely formed Charities and Societies shall have no legal personality.
2. Upon registering and thus acquiring legal personality, the rights and duties of the Charity or Society formed shall accrue to the registered Charity or Society.
3. Charities and Societies may not solicit money and property exceeding fifty thousand birr before its registration;
4. Failure to register within the prescribed period shall be a ground for cessation of the formed Charity or Society.

**፷፮. የዘርፍ አስተዳዳሪዎች**

፩. አግባብነት ያላቸው የፌዴራል አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የዘርፍ አስተዳዳሪ ሆነው በሚኒስትሩ ይሰየማሉ፡፡

፪. ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በአንድ የተወሰነ የዘርፍ አስተዳዳሪ የማይሸፈን ወይም ከአንድ በላይ የዘርፍ አስተዳዳሪን የሚመለከት ከሆነ ኤጀንሲው የዘርፍ አስተዳዳሪ ይሆናል፡፡

፫. ማናቸውም የዘርፍ አስተዳዳሪ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባር ለእርሱ ተጠሪ ለሆኑ የፌዴራል መንግስት አካላት በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

**፷፯. የዘርፍ አስተዳዳሪዎች ሥልጣንና ተግባራት**

የዘርፍ አስተዳዳሪዎች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖራቸዋል፤

፩. በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ምዝገባ ሂደት ለኤጀንሲው አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

፪. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሚገመግሙና አስተያየት የሚሰጡ ባለሙያዎችን ይመድባል፤

፫. በማቋቋሚያ ሕጉ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እና ከበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ጋር በሚገቡት ስምምነት መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን የሥራ እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፤

፬. የዘርፍ አስተዳዳሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት የወሰደውን እርምጃ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ለኤጀንሲው ያሳውቃል፤

፭. ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት

***66. Sector Administrators***

1. Relevant Federal Executive Organs shall be assigned by the minister as Charities and Societies Sector Administrators.
2. For the purposes of this proclamation the Agency shall be a sector administrator for charities or societies that do not fall under any sector administrator or fall under more than one sector administrator.
3. Any sector administrator may delegate powers and functions given to it under this proclamation to the relevant organs of federal government accountable to it.

***67. Powers and Functions of Sector Administrators***

Sector Administrators shall have the following powers and functions:

1. provides necessary support to the Agency in the process of registration of Charities and Societies;
2. assigns professionals who evaluate and recommend on the Charities' and Societies' programs and projects;
3. supervises and controls operational activities of Charities and Societies and take necessary measures according to laws establishing it and its agreements with the Charities and Societies;
4. A Sector Administrator taking measure by virtue of this Article shall notify the Agency of such measures within seven working days;
5. Develop criteria that have to be followed by

ሥራዎች ህብረተሰቡ የላቀ ተጠቃሚ መሆኑን ለማረጋገጥ ኤጀንሲው ሊከተላቸው የሚገቡ መስፈርቶችን ያወጣል፡፡

፮. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና የዘርፍ አስተዳዳሪውን የጋራ ግቦች ለማሣካት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ተቀናጅተው የሚሰሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ምዝገባ

### ፷፰. ምዝገባ

፩. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፱ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው ማመልከቻ ሲቀርብለት በ፴ ቀናት ውስጥ በዚህ አዋጅ የተደነገጉት አስፈላጊ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ አመልካቾቹን በበጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም በማህበርነት በመመዝገብ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ኤጀንሲው የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካልሰጠ ወይም የማይሰጥ መሆኑን ካላሳወቀ አመልካቹ በንዑስ አንቀጹ ከተቀመጠው የመጨረሻ ቀን በ፲፭ ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ ኤጀንሲው በሚያዘጋጀው ፎርም መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን ግብ፣ አላማና ሥራ የሚመለከቱ መግለጫዎችን የያዘ ሆኖ ከሚከተሉት ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፤

ሀ. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ እና እንደአስፈላጊነቱ የዘለቄታ በጎ አድራጎት

the Agency which shall assure the maximum benefits of the public from the activities of Charities and Societies;

6. may make arrangements with Charities for coordinated efforts towards the achievement of the common goals of the Charities and the said Sector Administrator.

## Sub-Section Two

## Registration of Charities and Societies

### 68. *Registration*

1. Subject to Article 69, the Agency shall, upon application and after ensuring the fulfillment of the requirements stipulated under this Proclamation, register the applicants as a Charity or a Society and issue a certificate of legal personality within 30 days from the date of application.
2. Where the Agency does not issue a certificate of legal personality or does not make known that it will not do the same the applicant may apply to the Board not later than 15 days from the last date of the time limit prescribed in the Sub-article.
3. An application for registration under this Article shall include particulars concerning its goals, objectives and activities as per the form prepared by the Agency accompanied by:

a. a copy of the rules of the Charity or the Society and where applicable a document showing the act of constituting of a

ድርጅቱን ወይም የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ያቋቋመው ሠነድ ቅጂ፤

ለ. እንዳስፈላጊነቱ ኤጀንሲው የሚጠይቃቸው ሌሎች ሠነዶች::

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ከተደነገጉት አስፈላጊ ሁኔታዎች በተጨማሪ ውጪ አገር የተመሰረተ የበጎ አድራጎት ድርጅት የሚከተሉትን ማቅረብ ይኖርበታል፤

ሀ. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ መቋቋሙን የሚያሳይ ከተቋቋመበት አገር የተሰጠውን የተረጋገጠ ሰነድ፤

ለ. ሥልጣን ያለው የድርጅቱ አካል ድርጅቱ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሠራ ያሳለፈው የተረጋገጠ ውሣኔ፤

ሐ. ኢትዮጵያ ከሚገኝ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ከተቋቋመበት አገር ኤምባሲ ወይም ኤምባሲ ከሌለ ከተቋቋመበት አገር ስልጣን ባለው አካል የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፤

መ. ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፤

ሠ. የአገር ውስጥ ተወካዩ የተሰጠው የተረጋገጠ የውክልና ሥልጣን::

፭. በዚህ አንቀጽ መሠረት የምዝገባ ማመልከቻ ሲቀርብ ተገቢው የምዝገባ ክፍያ መፈጸም አለበት::

Charitable Trust or a Charitable Endowment;

b. such similar documents and duly completed forms as the Agency may require.

4. In addition to the requirements set forth under Sub-article (2), Charities that are established abroad shall present:

a. duly authenticated certificate of registration showing its establishment from its country of origin;

b. proof of the decision of its competent organ to operate in Ethiopia;

c. a letter of recommendation by the Embassy in which the Charity is incorporated or in the absence of such by a competent Government Organ in that country;

d. a letter of recommendation from the Ministry of Foreign Affairs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

e. power of attorney of the country representative.

5. The necessary registration fee shall be paid where an application for registration under this Article is made.

**፷፱. የምዝገባ ጥያቄን ስላለመቀበል**

ኤጀንሲው ከሚከተሉት አንዱ ምክንያት መኖሩን ካረጋገጠ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን አይመዘግብም፤

፩. ሊቋቋም የታሰበው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር መተዳደሪያ ደንብ በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን መስፈርቶች የማያሟላ ሆኖ ሲገኝ፤

፪. ሊቋቋም የታሰበው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሕገ-ወጥ ለሆነ ዓላማ፣ የሕዝብን ሠላም ለሚያደፈርስ ተግባር ወይም የኢትዮጵያን ደህንነትና መረጋጋት ለመጉዳት መጠቀሚያ ሊሆን ይችላል የሚያሰኝ በቂ ምክንያት ሲኖር፤

፫. የምዝገባ ማመልከቻው የዚህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን ድንጋጌዎች የማያሟላ ሲሆን፤

፬. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የሚመዘገብበት ስም ከሌላ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም ከማንኛውም ሌላ ተቋም ስም ጋር የሚመሳሰል ከሆነ ወይም የሕዝብን ሞራል ወይም ሕግን የሚቃረን ሲሆን፤

፭. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ስያሜ አገር አቀፋዊ ወይም ፌዴራላዊ ሆኖ የአባላት ጥንቅር ወይም የሥራ ቦታው ቢያንስ የአምስት ክልሎች ውክልና የሌለው ከሆነ።

**69. *Refusal of Application for Registration***

The Agency shall refuse to register a Charity or Society where one of the following reasons occur:

1. the rules of the proposed Charity or Society do not comply with the necessary conditions set by this proclamation;
2. the proposed Charity or Society is likely to be used for unlawful purposes or for purposes prejudicial to public peace, welfare or good order in Ethiopia;
3. the application for registration does not comply with the provisions of this law or any regulations made hereunder;
4. the name under which the proposed Charity or Society to be registered resembles the name of another Charity or Society or any other institution or is contrary to public morality or is illegal;
5. where the nomenclature of the Charity or Society is country wide and the composition of its members or place of business do not show the representation of at least five regional states.

**፸. በሥራ መሪነት መሥራት የማይችሉ ሰዎች**

ማንኛውም ሰው በአንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም በእነዚሁ ቅርንጫፎች በሥራ መሪነት መሥራት የማይችለው፤

፩. በማጭበርበር ወይም ታማኝነትን በማጓደል ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተቀጣ ከሆነ፤

፪. በማናቸውም ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የሲቪል መብቱን የተገፈፈና መብቶቹ ያልተመለሱለት ከሆነ፤

፫. በሕግ መሠረት ከችሎታ ማጣት የተነሳ መሥራት የማይችል ከሆነ፤

፬. በፍርድ ክልከላ የተደረገበት ከሆነ፤

፭. ኢትዮጵያ ውስጥ ከሌለና አለመኖሩ ለበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ትክክለኛ አስተዳዳር እንቅፋት የሚሆን ከሆነ።

**70. *Persons Who shall not Act as Officers***

No person shall act as an Officer of a Charity or Society or a branch thereof if that person:

1. has been convicted of a crime that involves fraud or other crimes that involve dishonest acts;
2. has been convicted of any crime as a result of which she/he has been deprived of her/his civil rights and her/his civil rights have not yet been restored;
3. is unable to act by reason of incapacity within the meaning of law;
4. has been interdicted by a court;
5. is ouside Ethiopia and his absence impedes the proper administration of the Charity or Society.

**፸፩. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መዝገብ**

፩. ኤጀንሲው ማንኛውንም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበርን በሚመለከት በየጊዜው የሚወስናቸው ዝርዝሮች የሚመዘገቡበት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መዝገብ ይይዛል፡፡

፪. የእንዲሁ ዓይነት ሠነድ ሙሉ ወይም ከፊል ግልባጭ በኤጀንሲው ዳይሬክተር ትክክለኛ ቅጂ ለመሆኑ የተመሠከረ ከሆነና የኤጀንሲው ማሕተም ከተደረገበት በማናቸውም የክርክር ሂደቶች በማስረጃነት ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

፫. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መዝገብ በኤሌክትሮኒክ መልክ ጨምሮ ኤጀንሲው አግባብ ነው ብሎ በሚገምተው መንገድ ተዘጋጅቶ ይቀመጣል::

፬. ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገቡትን፣ የታገዱትንና ከመዝገብ የተሠረዙትን የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት ዝርዝር በጋዜጣ ያወጣል::

**71.** ***Register of Charities and Societies***

1. The Agency shall keep a register of Charities and Societies in which shall be entered such particulars as it may from time to time determine of any Charities and Societies registered therein.
2. A copy of or extract from any such document certified to be a true copy or extract under the signature of the Director of the Agency and seal of the Agency shall be admissible in evidence in any proceedings.
3. The register of Charities and Societies may be prepared and kept in such manner as the Agency may think fit, including in electronic form.
4. The Agency shall, by notification in the Gazette, publish the list of Charities and Societies registered, suspended or cancelled under this proclamation.

**፸፪. የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ቅርንጫፍ**

፩. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር አስቀድሞ ኤጀንሲውን በማሳወቅ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ቅርንጫፍ ሊከፍት ይችላል::

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለሚከፈት ቅርንጫፍ የሚሰጠው ሥልጣን ራሱን የቻለ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የሚያደርገው ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በቂ ቁጥጥር እንዳያደርግት የሚያደርገው ሊሆን አይችልም::

**72.** ***Branch of a Charity or a Society***

1. Any Charity or Society may establish a branch based on its rules by giving prior notice to the Agency.
2. The powers of the branch of the charity or society established under Sub-article (1) of this Article shall not make it an independent Charity or Society or not adequately under the control of the charity or society.

**፸፫. ስያሜ፣ የሥራ ቦታ ወይም መተዳደሪያ ደንብ ስለመለወጥ**

፩. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ስያሜውን ወይም የሥራ ቦታውን ከለወጠ ወይም መተዳደሪያ ደንቡን ካሻሻለ ለውጡን ወይም ማሻሻያውን ለኤጀንሲው አቅርቦ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፰ መሠረት

**73.** ***Change of Name, Place of Work or Rules***

1. If a Charity or Society Changes its name, place of work or amends its rules, it shall submit the change or amendment and get it registered under Article 68 of this

ማስመዝገብ አለበት፡፡

፪. የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከተመዘገበ በኋላ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፱ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፫)፣ (፬) ወይም (፭) የተደነገገው በማናቸውም ምክንያት ሳይከበር መታለፉ ከተረጋገጠ ኤጀንሲው በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መተዳደሪያ ደንቡ እንዲሻሻል ወይም ጉድለቱ እንዲታረም ሊያዝ ይችላል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ መሠረት የተፈጸመ የስም ለውጥ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን ማናቸውንም መብቶች ወይም ግዴታዎች አይነካም፡፡ በቀድሞ ስሙ በእርሱ ወይም በራሱ ላይ ቀጥለው ወይም ተጀምረው የነበሩ ክርክሮች በአዲሱ ስም ይቀጥላሉ ወይም ይጀመራሉ፡፡

**፸፬. በምልክቶች ስለመጠቀም**

፩. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በኤጀንሲው ሳያስመዘግብ ማናቸውንም ምልክት መጠቀም አይችልም፡፡

፪. ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቀረበለትን ዓርማ ለመመዝገብ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፱ የተደነገጉትን የምዝገባ መመዘኛዎችን ግምት ውስጥ ያስገባል፡፡

**፸፭. የምስክር ወረቀትን በይፋ ስለ ማሣየትና ስለ ማስታወቂያ ሰሌዳ**

፩. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን በዋናው መሥሪያ ቤትና ግልባጩን በየቅርንጫፎቹ ለማናቸውም ጉብኚ ሊታይ በሚችል ቦታ ማስቀመጥ ይኖርበታል፤

፪. አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የማስታወቂያ ሠሌዳ የሚጠቀም ከሆነ ኤጀንሲው በመመሪያ የሚወስናቸውን ዝርዝሮች በሰሌዳው ላይ መለጠፍ ይኖርበታል፤

**፸፮. ፈቃድ ስለማሳደስ**

፩. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፰ እና ፹ መሠረት አመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርትና የሂሳብ መግለጫዎችን ለኤጀንሲው የማቅረብ ግዴታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ፈቃዳቸውን

proclamation.

2. The Agency may, after setting a reasonable time limit, order the amendment of the rule or correction of a fault where it is found that the provisions of Sub-articles (1), (3), (4) and (5) of Article 69 are not complied with.

3. A change of name by a Charity or Society under this Article shall not affect any rights or obligations of the Charity or Society; and any legal proceeding that might have been commenced by or against it in the former name may continue in its new name.

**74. *Use of Symbols***

1. No Charity or Society shall use any symbol without having registered such symbol by the Agency.
2. The Agency shall consider the the requirements of registration under Article 69 while registering a symbol under Sub-article (1) of this Article.

**75. *Display of Certificate and Use of Advertisement Boards***

1. Every Charity or Society shall keep its certificate of registration in its Head Office and a copy thereof in its branches in a place that is visible to any visitor.
2. Where a Charity or Society uses an advertisement board, it shall affix on such board those particulars as are determined by the directives of the Agency.

**76. *Renewal of License***

1. Whithout prejudice to the obligation of Charities to submit statements of accounts and annual reports as stipulated under Article 78 and 80 of this proclamation, the

በየሦስት ዓመቱ ማሳደስ አለባቸው::

፪. ፈቃድ የሚታደሰው በፈቃድና ምዝገባ ሰርተፊኬቱ ላይ የተገለፀው ጊዜ የሚያገለግልበት የመጨረሻ ቀን ካለፈ በኋላ ባሉት ሁለት ወራት ውስጥ ነው::

፫. ኤጀንሲው፣

ሀ. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የስራ አፈጻፀምና የኦዲት ሪፖርቶች የተሟሉና ትክክለኛ መሆናቸውን፣ እና

ለ. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ወይም በኤጀንሲው የተሰጡ ትዕዛዞችን ወይም የራሱን መተዳደሪያ ደንብ ያልጣሰ መሆኑን፣

ሲያረጋግጥና አስፈላጊው የማሳደሻ ክፍያ ከተፈጸመ በኋላ ፈቃዱን ያድሳል::

## ክፍል ስድስት
## ስለ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ሂሣብ እና ሪፖርቶች

### ፸፯. የሂሣብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ

፩. የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የስራ መሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን የገንዘብ እንቅስቃሴዎች የሚያብራራ እና በማናቸውም ጊዜ ሊያሣይ የሚችል የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለባቸው፤

፪. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የሂሣብ ሰነዶች የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የተቀበለውን ጠቅላላ ገንዘብና ያወጣውን ወጪ፣ የወጪውን ምክንያት፣ ሀብትና ዕዳ ያካተቱ መሆን አለባቸው፤

፫. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ስሙ ካልተገለፀ ሰው ልገሳ መቀበል አይችሉም:: በማናቸውም ጊዜ የለጋሹን ማንነት በግልጽ የሚያመለክቱ መዝገቦችን መያዝ አለባቸው::

፬. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ የሥራ መሪዎች በዚህ አንቀጽ መሠረት የተዘጋጁ የሂሳብ ሰነዶችን ሰነዶቹ የተዘጋጁበት የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ የሂሣብ ዓመት ካለቀ በኋላ ቢያንስ ለ፭ ዓመታት ጠብቀው ማቆየት

license of Charities shall be renewed every three years.

2. The license shall be renewed not later than two months after the expiry date mentioned on the license and registration certificate.
3. The Agency shall renew the license of Charities upon payment of renewal fees and when it ensures that;
   a. the performance and audit reports are complete and accurate;
   b. the Charity has not violated the provisions of this Proclamation or Regulations or directives issued thereunder.

## SECTION SIX
## CHARITY AND SOCIETY ACCOUNTS AND REPORTS

### 77. *Duty to Keep Accounting Records*

1. The Officers of a Charity or Society shall ensure that accounting records are kept inrespect of the Charity or Society which are sufficient to show and explain all the transactions and disclose at any time.
2. The accounting records shall, in particular, contain entries showing from day to day all sums of money received and expended by the Charity or Society, and the matters in respect of which the receipt and expenditure takes place; and record of the assets and liabilities of the Charity or Society.
3. Charities and Societies may not receive anonymous donations and shall at all times keep records that clearly indicate the identity of donors.
4. The Officers of a Charity or Society shall preserve any accounting records made for the purposes of this Article for at least 5 years from the end of the financial year of the Charity or Society in which they are made.

አለባቸው::

፭. ኤጀንሲው ሰነዶቹ እንዲወድሙ ወይም በሌላ መንገድ እንዲወገዱ በጽሁፍ ካልፈቀደ በስተቀር ከሂሳብ ሰነድ ጋር በተያያዘ በንዑስ አንቀጽ (፬) የተገለጸው አምስት ዓመት ከማለቁ በፊት የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ሕልውና ካከተመ የሂሳብ ሰነዶቹን ጠብቆ የማቆየት ግዴታ በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም በማህበሩ ቀሪ የስራ መሪዎች ተፈጻሚ መሆኑ ይቀጥላል::

### ፸፰. ዓመታዊ የሂሣብ መግለጫ

፩. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ተቀባይነት ባላቸው መመዘኛዎች መሰረት የተዘጋጀ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ ለኤጀንሲው በአድራሻ መላክ አለበት::

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም የሚያንቀሳቅሱት ገንዘብ ከብር ፶፻፻ የማይበልጥ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ገቢን፣ ወጪን፣ ሃብትንና ዕዳን የሚያመለክት መግለጫ ብቻ ማቅረብ ይችላሉ።

፫. የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የሥራ መሪዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት የተዘጋጀ የሂሣብ መግለጫና ተያያዥ ሰነድ የበጀት ዓመቱ ካበቃበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ ለአምስት ዓመታት ጠብቀው ያቆያሉ::

### ፸፱. ዓመታዊ የሂሣብ ምርመራ ስለማድረግ

፩. የማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሂሣብ በየዓመቱ በተመሰከረለት ኦዲተር ወይም የውስጥ ኦዲተር ወይም ኤጀንሲው በሚሾመው ኦዲተር መመርመር አለበት::

፪. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በውጭ ኦዲተር የመመርመር ግዴታ የሚኖርበት አግባብነት ባለው የበጀት ዓመት ቀድሞ ያለው የበጀት ዓመት ሂሳብ

5. Unless the Agency consents in writing to the records being destroyed or otherwise disposed of, where a Charity or Society ceases to exist within the period of 5 years mentioned in Sub-article (4) as it applies to any accounting records, the obligation to preserve those records in accordance with that Sub-article shall continue to be discharged by the last officers of the Charity or Society.

### 78. *Annual Statements of Accounts*

1. Any Charity or Society shall submit to the Agency an annual statement of accounts prepared in accordance with acceptable standards.
2. Notwithstanding Sub-article (1) of this Article, Charities and Societies whose annual flow of funds does not exceed Birr 50,000.00, the statement of accounts may choose to prepare a receipts and payments account and a statement of assets and liabilities.
3. The Officers of a Charity or Society shall preserve any statement of accounts and related documents prepared under Sub-article (1) and (2) of this Article for at least 5 years from the end of the financial year.

### 79. *Annual Examination of Accounts*

1. Any Charity's or Society's account shall be examined annually by a Certified Auditor or internal auditor or an auditor designated by the Agency.
2. Any Charity or Society shall be audited by an External Auditor where its annual gross income immediately preceding the specified budget year is more than Birr 100,000.00.
3. Notwithstanding Sub-article (2) of this

ከብር ፻፻፻ የሚበልጥ ሲሆን ነው።

፫. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ቢኖርም ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ማንኛውም ዓይነት የሂሳብ ምርመራ በማንኛውም ጊዜ በውጭ ወይም በውስጥ ኤጀንሲው በሚሾመው ኦዲተር ሊመረመር ይችላል።

፬. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ ሂሣብ ዓመቱ ባለቀ አምስት ወራት ውስጥ ካልተመረመረ ወይም በውጭ ኦዲተር ማስመርመር የተሻለ ሆኖ ሲገኝ ኤጀንሲው ኦዲተር ሾሞ ማስመርመር ይችላል።

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት በኤጀንሲው በተሾመው ኦዲተር ለተከናወኑ ማናቸውም የኦዲት ሥራዎች ወጭ የሚከፍለው የሚመለከተው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም ጥፋተኛ ሆነው ሲገኙ የስራ መሪዎቹ ይሆናሉ።

## ፹. ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት

፩. የሥራ መሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች ማህበርን የእያንዳንዱን የበጀት ዓመት ዋና ዋና ክንዋኔዎች ሪፖርትና አስፈላጊ መረጃ በማዘጋጀት ለኤጀንሲው ማቅረብ አለባቸው።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ሪፖርት የሂሣብ ዓመቱ ባለቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ እንዲሁም ኤጀንሲው በማናቸውም ልዩ ምክንያት በሚጠይቀው ጊዜ ውስጥ የሥራ መሪዎቹ ለኤጀንሲው ማቅረብ አለባቸው።

፫. ማንኛውም የሥራ ክንውን ሪፖርት ለኤጀንሲው ሲደረግ የሂሣብ መግለጫ አብሮ መያያዝ አለበት።

## ፹፩. ዓመታዊ ሪፖርት ለሕዝብ ክፍት ስለማድረግ

በኤጀንሲው ዘንድ የሚገኝ ማናቸውም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት የዓመት ሪፖርት ወይም ሌላ ሠነድ ጉዳዩ በሚመለከተው አካል ወይም በኤጄንሲው ወይም በሚመለከተው

Article, examination of account may be conducted by an external or internal auditor or an auditor designated by the Agency any time according to the directives issued by the minister.

4. Where it appears to the Agency that the account of a Charity or Society is not audited within five months from the end of that year or to be audited by a certified external auditor, the Agency may appoint an Auditor.
5. In accordance with Sub-article (4) of this Article, the expenses of any audit carried out by an Auditor appointed by the Agency shall be paid by the Charity or Society concerned, or where at faults the Officers of the Charity or Society.

## 80. *Annual Activity Report*

1. The Officers of a Charity or Ethiopian Resident Society shall prepare and transmit to the Agency an annual activity report on the major activities and relevant information regarding the Charity or Society.
2. The annual activity report required under Sub-article (1) of this Article shall be transmitted to the Agency within three months from the end of that financial year or within such period as the Agency may for any special reason require.
3. Every such annual activity report shall have attached to it the annual statement of accounts.

## 81. *Disclosure of Annual Activity Report*

Any annual activity report or other document kept by the Agency, when requested by a concerned body, may be made open to the public at any reasonable time if the Agency or

የዘርፍ አስተዳዳሪ ወይም በበጎ አድራጎት ድርጅቱ እና ማህበሩ ውሳኔ በማናቸውም አመቺ ጊዜ ለህዝብ ክፍት ሊደረግ ይችላል፡፡

**፹፪. ለሌሎች ሰዎች ሪፖርት ስለማድረግ**

የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች የማህበሩ ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የመተዳደሪያ ደንብ በዚህ ክፍል ከተጠቀሱት አካላት በተጨማሪ ለሌሎች ሰዎች ወይም ድርጅቶች የሂሳብ መዛግብት፣ የኦዲት ሪፖርቶች እና ዓመታዊ ሪፖርት ማቅረብን አይከለክልም፡፡

**፹፫. የባንክ ሂሳብ ስለማስታወቅ**

የበጎ አድራት ድርጅት ወይም የማህበር መሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን የባንክ ሂሳብ ከሚፈለገው ዝርዝር ጋር ለኤጀንሲው በየአመቱና በተጠየቁ ጊዜ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

## ክፍል ሰባት

## የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን ስለመቆጣጠር

**፹፬. ምርመራ የማድረግ ሥልጣን**

፩. ኤጀንሲው በየጊዜው ለአጠቃላይ ወይም ለአንድ የተወሰነ ጉዳይ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ወይም ማህበራትን ወይም የተወሰኑ ወይም አንድ ዘርፍ የሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ወይም ማህበራትን የተመለከተ ምርመራ ሊያካሂድ ይችላል፡፡

፪. ለእንዲህ ዓይነት ምርመራ ጉዳይ ኤጀንሲው ማናቸውንም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም የሥራ መሪ ወይም ሠራተኛ፤

ሀ. የሚያውቀውን ወይም መረጃ ሊያገኝ የሚያስችለው ምክንያታዊ ግምት ኖሮ ምርመራው የሚካሄድበትን ጉዳይ

the Sector Administrator or the Charity and Society so decide.

**82.** ***Reporting to other Persons***

Nothing in this part shall prohibit the rules of a Charity or Society from requiring that books of account, audit reports and annual reports be submitted to persons or organizations in addition to which reports are made under this part.

**83.** ***Notification of Bank Accounts***

The officers of a Charity or Society shall report to the Agency annually and upon request about all the bank accounts of the Charity or Society with necessary particulars.

## SECTION SEVEN

## SUPERVISION OF CHARITIES AND SOCIETIES

**84.** ***Power to Institute Inquiries***

1. The Agency may from time to time institute inquiries with regard to Charities or Societies or a particular Charity or Society or class of charities or societies, either generally or for particular purposes.
2. For the purposes of any such inquiry, the Agency may by order require any Charity or Society or an officer or employee thereof:
   a. to furnish accounts and statements in writing with respect to any matter in question at the inquiry, being a matter on which that person has or can

በተመለከተ ሂሣብና መግለጫ በጽሁፍ እንዲሰጥ፣ ጉዳዩን በተመለከተ ለቀረበለት ጥያቄ ወይም ምርመራ በጽሁፍ መልስ እንዲሰጥ፤

ለ. በምርመራው ሂደት መመርመር ያለበትን ማናቸውንም ጉዳይ በተመለከተ በእጁ ወይም በቁጥጥሩ ሥር ያሉትን ሠነዶች ቅጂ እንዲሰጥ፤

ሐ. በተወሰነ ጊዜና ቦታ በመገኘት ማስረጃ ወይም ሠነዶችን እንዲያቀርብ፣

ሊያዝ ይችላል::

፫. ኤጀንሲው ምርመራ በሚያካሂድበት ወቅት ከሕዝብ የሚቀርቡ ጥቆማዎችን፣ ከመንግሥት አካላት የሚቀርቡ ሪፖርቶችን እና ከበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ከማህበራት ከራሣቸው የሚቀርቡ ሪፖርቶችን ጨምሮ ማናቸውንም የመረጃ ምንጭ ሊጠቀም ይችላል::

reasonably obtain information, or to return answers in writing to any questions or inquiries addressed to him on any such matter;

b. to furnish copies of documents in his custody or under his control which relate to any matter in question at the inquiry;

c. to attend at a specified time and place and give evidence or produce documents.

3. The Agency may use, for the purpose of the inquiry, any source of information including reports from the public, reports from government agencies including the reports of Charities and Societies.

### ፹፭. <u>ሠነዶች እንዲያቀርቡ የማዘዝና ሪከርዶች እንዲመረመሩ የማድረግ ሥልጣን</u>

፩. ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን በሥራ ላይ ለማዋል ከአንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም የሥራ መሪ ወይም ሠራተኛ፤

ሀ. አንድን የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የሚመለከት በይዞታው ሥር ያለ ማንኛውንም መረጃ በጽሁፍ ወይም በቃል ለኤጀንሲው እንዲሰጥ፤ ወይም

ለ. የሠነዱን ሙሉ ወይም ከፊል ግልባጭ ለኤጀንሲው እንዲሰጥ፤ ወይም

ሐ. ሠነዱ የአንድ ፍርድ ቤት ወይም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሪከርድ ወይም ሠነዶች አካል ካልሆነ በስተቀር ሠነዱን ራሱን ለምርመራ ለኤጀንሲው እንዲሰጥ፤

በትዕዛዝ ሊጠይቅ ይችላል::

፪. ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ማናቸውንም ግልባጭ ወይም የሠነድ ክፍል ያለ ክፍያ የማግኘት

### 85. *Power to Cause the Production of Documents and Search Records*

1. The Agency may, for the purpose of discharging its functions under this Proclamation, by order, require any Charity or Society or an officer or employee thereof:
   a. to furnish orally or in writing the Agency with any information in her/his possession which relates to any Charity or Society; or
   b. to furnish the Agency with a copy of or extract from the document ; or
   c. to transmit the document itself to the Agency for its inspection unless the document forms part of the records or other documents of a court or public authority.
2. The Agency shall be entitled without payment to keep any copy or extract furnished to it under Sub-article (1) of this Article.

ሥልጣን አለው::

**፹፮. ስብሰባዎችን ስለማስታወቅ**

ማንኛውም ማህበር የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ከመካሄዱ ከሰባት የሥራ ቀናት አስቀድሞ የስብሰባውን ጊዜና ቦታ ለኤጀንሲው በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት::

**፹፯. መረጃ ስለመግለጽ**

በሌሎች ሕጐች በግልጽ የተደነገጉት ክልከላዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኤጀንሲው ወይም የዘርፍ አስተዳዳሪው ሥራዎቹን በሚገባ እንዲያከናውን ለማስቻል ወይም ለመርዳት ማንኛውም ሰው ያገኛቸውን ማናቸውንም መረጃ ለኤጀንሲው ወይም ለዘርፍ አስተዳዳሪው መግለጽ ይችላል::

**፹፰. የአስተዳደራዊና የዓላማ ማስፈጸሚያ ወጪዎች**

፩. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በየበጀት ዓመቱ ከሚያወጣው ወጪ ከ ፸ በመቶ የማያንሰውን ዓላማውን ለማስፈጸም እና ከ ፴ በመቶ የማይበልጠውን ለአስተዳደራዊ ሥራ ማዋል አለበት::

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ቢኖርም ከጠቅላላ ገቢው ከ ፹ በመቶ በላይ ለዓላማው ማስፈጸሚያ ለሚያውል ወይም የላቀ የሥራ አፈጻጸም ላሳየ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር መንግሥት የተለያዩ ማበረታቻዎችን ሊያደርግ ይችላል::

**፹፱. የውጭ ዜጎችን ስለ መቅጠር**

፩. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የሥራ ፈቃድ ያልተሰጠውን የውጪ ዜጋ መቅጠር አይችልም::

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት

**86.** ***Notification of Meetings***

Any Society shall notify the Agency in writing of the time and place of any meeting of the General Assembly of the Society not later than seven working days prior to such meeting.

**87.** ***Disclosure of Information***

Subject to any express restriction imposed under any other law any person may disclose to the Agency or to any sector administrator any information received by him for the purpose of enabling or assisting the Agency or the sector administrator to discharge its functions.

**88.** ***Administrative and Operational Costs***

1. Any charity or society shall allocate not less than 70 percent of the expenses in the budget year for the implementation of its purposes and an amount not exceeding 30 percent for its administrative activities.
2. Notwithstanding subarticle (1) of this Article, the government may confer various incentives to a charity or society that allocate more than 80% of its total income for its operational purposes or demonstrates outstanding performance.

**89.** ***Employment of Expatriates***

1. No Charity or Society shall employ expatriates unless a work permit is granted in accordance with the relevant law.
2. Notwithstanding the provision of Sub-article (1) of this Article there shall be no restriction on the entitlement of Foreign Charities to designate country

የውጭ ዜጋን የሀገር ውስጥ ተወካይ አድርጎ ለመመደብ ገደብ አይኖርበትም፡፡

**፺. የንብረት ጥበቃ**

፩. ኤጀንሲው ማንኛውንም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በተመለከተ በሚያደርገው ክትትል ወይም ምርመራ ተገቢ ያልሆነ የሥራ አመራር ወይም ድርጊት መፈጸሙን ሲያረጋግጥና የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን ንብረት ለመጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ ይችላል፤

ሀ. ተገቢ ላልሆነው የሥራ አመራር ወይም ድርጊት ሃላፊ የሆነውን የሥራ መሪ ማገድና ሥልጣን ያለው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ተተኪ እንዲመድብ ያዛል፤

ለ. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የአሠራር ሥርዓቱን እንዲያሻሽል ያዛል፤

፪. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሀ) ወይም (ለ) መሠረት የተሰጠውን ትዕዛዝ ተግባራዊ እስከሚያደርግ ድረስ፣

ሀ. ያለ ኤጀንሲው ፈቃድ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን የተወሰኑ ግዴታዎች ውስጥ የሚያስገቡ ውሎች እንዳይደረጉ ወይም የተወሰኑ ዓይነት ክፍያዎች እንዳይፈጸሙ ያግዳል፤

ለ. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ ንብረት በይዞታው ስር ያለን ሰው ወይም ባለዕዳን ያለ ኤጀንሲው ፈቃድ ንብረቱን እንዳይመልስ ወይም ዕዳውን እንዳይከፍል ያግዳል ወይም ኤጀንሲው በሚወስነው ቦታ ወይም ባንክ እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡

**፺፩. የስራ መሪዎችን ስለ ማንሳትና መተካት**

፩. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የማህበር መሪ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸ ከተመለከቱት መመዘኛዎች አንዱን ያጓደለ እንደሆነ ሥልጣን ባለው የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ አካል እንዲነሳና በሌላ እንዲተካ እንዲደረግ ኤጀንሲው ያዛል፡፡

representatives.

**90. *Protection of Property***

1. Where, at any time the Agency has upon an inquiry or investigation with respect to any Charity or Society and is satisfied that there is or has been any misconduct or mismanagement in the administration of the Charity or Society and where it is necessary to act for the purpose of protecting the property of the Charity or Society the Agency may take the following measures:
   a. suspend the officer responsible for the misconduct or mismanagement and order the appropriate organ of the Charity or Society to assign another person;
   b. order the Charity or Society to improve its system of operation.
2. Until the Charity or Society acts upon the Agency's orders given pursuant to Sub-articles (1) (a) and (b) of this Article, the Agency may:
   a. prevent the Charity or Society from entering into certain obligations or making certain types of payments;
   b. order any person who holds any property on behalf of the Charity or Society or any debtor, not to part with the property or not to pay his debt without the approval of the Agency or to deposit the payment in a certain place or bank.

**91. *Removal and Replacement of Officers***

1. The Agency may order the appropriate organ of the Charity or Society to remove an officer who falls short of any of the requirements set forth under Article 70 and to assign another person as an officer.
2. Until the replacement an officer mentioned

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው የሥራ መሪ በሌላ እስኪተካ ድረስ ከሃላፊነት እንዲታገድ ኤጀንሲው ሊያዝ ይችላል::

## ፺፪. ፈቃድ ስለማገድና ስለመሰረዝ

፩. ማናቸውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር፣

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፫(፪) መሠረት የተላለፈውን የኤጀንሲውን ትዕዛዝ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሳይፈጽም ከቀረ፣

ለ. ያቀረበው ሪፖርት ሀሰተኛ ከሆነ፣

ሐ. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪(ሐ) እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ወይም በኤጀንሲው የተሰጡ ትዕዛዞችን ወይም የራሱን መተዳደሪያ ደንብ የጣሰ እንደሆነ፣

መ. በዚህ አዋጅ መሠረት ለኤጀንሲው ማቅረብ የሚገባቸውን መረጃዎች በወቅቱ ያላቀረበ እንደሆነ፣ጉድለቶቹን እስከሚያስተካክል ድረስ ፈቃዱ በኤጀንሲው ሊታገድ ይችላል::

፪. ማናቸውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር፣

ሀ. የተመዘገበው በማታለል ወይም በማጭበርበር ከሆነ፣ ወይም

ለ. ሕገወጥ ለሆነ ዓላማ፣ ወይም የሕዝብን ሠላምና የአገርን ደህንነት ለሚጎዱ ዓላማዎች ውሎ ከሆነ፤

ሐ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለዕግድ ምክንያት የሆኑትን ጉድለቶች ኤጀንሲው በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላስተካከለ፣ ወይም

መ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፮ መሠረት

under sub article 1 of this article by another officer, the Agency may order the suspension of an officer.

## 92. *Suspension and Cancellation of License*

1. Any Charity or Society:

   a. that fails to comply with the Agency's orders under Article 73(2) of this proclamation within the time limit set by the Agency;
   b. that has submitted falsified accounts and reports to the Agency;
   c. without prejudice to Sub-article 2(c) of this Article that contravenes the provisions of this Proclamation or Regulations and Directives issued thereunder or orders of the Agency or its own rules;
   d. that fails, within the appropriate time, to provide the Agency with information required by this Proclamation; may be suspended by the agency until it comes into compliance.

2. The license of any Charity or Society shall be canceled where:

   a. its registration has been procured by fraud or misrepresentation;
   b. it has been used for unlawful purposes or for purposes prejudicial to public peace, welfare or security;
   c. it fails to rectify the causes for suspension within the time limit set by the Agency in accordance with Sub-article (1) of this proclamation; or
   d. it fails to renew its license in accordance with Article 76 of this proclamation;

ፈቃዱን ካላሳደሰ፣

ሠ. የወንጀል ሕጉን ወይም የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመጣስ የወንጀል ድርጊት ከፈጸመ፤

ፈቃዱ ይሰረዛል።

e. It commits a crime by violating the provisions of the criminal code or that of this proclamation.

**፺፫. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መፍረስ**

፩. የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በሚከተሉት ምክንያቶች በኤጀንሲው ሊፈርስ ይችላል፤

ሀ. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ሥልጣን ያለው አካል በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት እንዲፈርስ ሲወስን፤

ለ. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፪ መሠረት በኤጀንሲው ሲሠረዝ፤ ወይም

ሐ. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ዕዳውን የመክፈል ችሎታ የሌለው ሲሆን።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት የሚፈርሱት በፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ነው።

**93. *Dissolution of Charities and Societies***

1. A Charity or Society may be dissolved by the Agency where:

   a. the appropriate organ of the Charity or Society decides to dissolve it in accordance with its rules;

   b. the Agency cancels the license of the Charity or Society in accordance with Article 92 of this proclamation; or

   c. the Charity or Society has become insolvent.

2. The dissolution of Ethiopian Charities and Societies in accordance with Sub-article (1) of this Article shall be effected by the decision of the Federal High Court.

**፺፬. የመፍረስ ውጤት**

፩. የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር እንዲፈርስ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ሲሰጥ፤

ሀ. ንብረቱ ወዲያውኑ የማፍረሱ ውሳኔ በተሰጠበት ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ የማፍረስ ሂደቱን እንዲያከናውን በተሾመው ሂሣብ አጣሪ ኃላፊነት ስር ይሆናል፤

ለ. ሂሣብ አጣሪው የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን እዳዎችና ኃላፊነቶች እንዲሁም የማፍረስ ሂደቱን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ወጪዎች ተጠናቀው ከተከፈሉ በኂላ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ቀሪ ገንዘብ ወይም ንብረት ካለ ተመሣሣይ ዓላማ ላለው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ለማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር

**94. *Effects of Dissolution***

1. Where an order or decision of dissolution against any Charity or Society is given:

   a. the property of Charity or Society shall forthwith vest in the liquidator appointed for the purpose of winding up in the dissolution order or decision;

   b. the liquidator or that other officer shall proceed to wind up the affairs of the Charity or Society and, after satisfying and providing for all debts and liabilities of the Charity or Society and the costs of winding up, shall transfer the surplus assets, if any, of the Charity or Society to a Charity or Society with a similar purpose or to any Charity or Society by

እንዲተላለፍ ኤጀንሲው ትዕዛዝ ይሰጣል፤

፪. የፈረሰ የበጎ አድራጎት ድርጅትን ወይም ማህበርን የሂሣብ አጣሪ መሾም በተመለከተ ኤጀንሲው ወይም ፍርድ ቤት የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የሥራ መሪዎችን ወይም ማኛውንም ሰው ሊሾም ይችላል፡፡

፫. ሂሳቡ በመጣራት ላይ ያለ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከዓላማው ጋር የተያያዙና ሊቋረጡ የማይችሉ ሥራዎችን ኤጀንሲውን በማስፈቀድ ለማጠናቀቅ ካልሆነ በስተቀር ከሂሳብ ማጣራቱ ውጭ ሌላ ተግባር ማከናወን አይችልም፡፡

፬. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ የሂሳብ ማጣራት ሥራዎች ተጠናቀው ምዝገባው እስከሚሰረዝ ድረስ ሕጋዊ ሰውነቱን እንደያዘ ይቆያል፡፡

## ክፍል ስምንት
## ንብረትን ለተቀራራቢ ዓላማ ማዋል

**፺፭. ንብረትን ለተቀራራቢ ዓላማ ማዋል ስለሚፈፀምባቸው ሁኔታዎች**

፩. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የመጀመሪያ ዓላማ ሊለወጥ የሚችልባቸውና የተሰጠው ሙሉ ንብረት ወይም ክፊሉ ለሌላ ተቀራራቢ ዓላማ እንዲውል በሚከተሉት ሁኔታዎች ይፈጸማል፤

ሀ. የመጀመሪያው ዓላማ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሲሳካ ወይም የማይሳካ ወይም ሊሳካ የማይችል ሲሆን፤

ለ. ድርጅቱ ለመጀመሪያው ዓላማ ካለው ንብረት ከፊሉ ብቻ በጥቅም ላይ እንዲውል የሚያመለክት ሲሆን፤

ሐ. ለበጎ አድራጎት ድርጅቱ የተሰጠ ስጦታ መንፈስ ሳይነካ በስጦታው መሠረት ያለው ንብረት እና ለተመሣሣይ ዓላማ የሚውል ሌላ ንብረት እና ቢቀናጁ አመቺ በሆነ ሁኔታ የበለጠ ውጤታማ በሆነ መንገድ ለጋራ ዓላማዎች ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ሲሆን፡፡

፪. የዘለቄታ በጎ አድራጎት ወይም የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ማቋቋሚያ ጉዳዩ በሚመለከታቸው የሥራ መሪዎች ላይ ሁኔታው በሚያስገድድበት ጊዜ ንብረቱ ወይም ከፊሉ ለተቀራራቢ ዓላማ ማዋል

the order of the Agency.

2. The Agency or the court may appoint the officers of a Charity or Society as liquidators for the Charitiy or Society dissolved.

3. A Charity or Society that is being dissolved shall not perform activities other than those necessary for its liquidation unless the Agency authorizes it to undertake activities that are related to its objectives and cannot be discontinued.

4. The Charity or Society shall retain its legal personality until its liquidation is complete and its registration is cancelled.

## SECTION EIGHT
## APPLICATION OF PROPERTY CY-PRÈS

**95. *Conditions for Applying Property Cy-près***

1. The circumstances in which the original purposes of a Charity can be altered to allow the property given or part of it to be applied cy-près shall be as follows:

   a. where the original purposes in whole or in part have been fulfilled or cannot be fulfilled or impossible to fulfill;
   b. where the original purposes provide a use for part only of the property available to the Charity;
   c. where the property available by virtue of the gift and other property applicable for similar purposes can be more effectively used in conjunction and to that end can suitably, regard being had to the spirit of the gift, be made applicable to common purposes;

2. An act of endowment or trust for charitable purposes places the concerned officers under a duty, where the circumstances require the property or some part of it to be applied cy-près, to secure its effective use for Charity

እንዲፈጸምበት ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው፡፡

፫. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የሥራ መሪዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ስር የተጠቀሱትን ተግባራት ሊፈፅሙ የሚችሉት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ውሳኔ ሲያስተላልፉ ብቻ ነው፡፡

፬. ንብረቱ የተሰጠው ይህ አዋጅ ተፈጻሚ ከመሆኑ በፊት ቢሆንም ይህ አንቀጽ ለበጐ አድራጐት ዓለማዎች በተሰጠ ንብረት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚከናወኑ ተግባራት ተፈጻሚነት የሚኖራቸው በኤጀንሲው ሲጸድቅ ብቻ ነው፡፡

**፺፮. <u>የማቋቋሚያ ሰነድ ወይም ትዕዛዝ መመሪያዎች</u>**

፩. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት አደራ ጠባቂ ወይም የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት ቦርድ ድርጅቱን ካቋቋመው ሰነድ ወይም ትእዛዝ የተቀበላቸውን ግልጽ የሆኑ መመርያዎችን መከተል አለበት፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በአደራ ወይም የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት ተጠቃሚ ለሆነው ሰው ጥቅም የሚያስፈልግ ሆኖ የታየ እንደሆነ ከተባሉት መመሪያዎች ውጭ ለመስራት አደራ ጠባቂው ወይም ቦርዱ ከኤጀንሲው ፈቃድ መጠየቅ ይችላል፡፡

**፺፯. <u>የአነስተኛ በጎ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ልዩ ድንጋጌዎች</u>**

፩. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ በመጨረሻው የሒሣብ ዓመቱ ጠቅላላ ገቢው ከ፶፻፻ (ሃምሳ ሺህ) ብር በላይ ካልሆነና የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት ካልሆነ በስተቀር የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የበላይ አካል የሚከተሉትን ሊፈጽም ይችላል፤

ሀ. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ሁሉም ንብረቶች ለሌላ የበጎ አድራጎት ድርጅት እንዲተላለፍ ወይም እንዲከፋፈል፤

by taking steps to enable it to be so applied.

3. The competent officers of a Charity may take the actions provided for in Sub-article (1) of this Article only by a two thirds majority decision.

4. This Article shall apply to property given for charitable purposes, notwithstanding that it was so given before the effective date of this Proclamation.

5. The provisions of this Article shall apply only upon the prior approval of the Agency.

**96. *Directions of the Constitutive Instrument or Act***

1. The trustee or board shall conform to the express instructions of the instrument or act constituting the Charitable Trust or Endowment.
2. Irrespective of the provision of Sub-article (1) of this article where the interests of the beneficiaries of a Charitable Trust or an Endowment so require, the trustee or the board may obtain an authorization from the Agency to depart from such instructions.

**97. *Special Provisions to Small Charities and Societies***

1. Where the gross income of a Charity in its last financial year does not exceed Birr 50,000.00 (fifty thousand) and it does not own any immovable property, the competent organs of the Charity may decide that:
   a. all the property of the Charity should be transferred or divided to such other charities ;

ለ. የመተዳደሪያ ደንቡ ሁሉንም ወይም ማናቸውንም የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ዓላማዎች በጎ አድራጎት ወደሆኑ ሌሎች አላማዎች በመለወጥ እንዲሻሻል ማድረግ፤

ሐ. የስራ መሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቱን በማስተዳደር ረገድ ሊከተሏቸው የሚገቡ ስነሥርዓቶችን በተመለከተ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብ እንዲሻሻል ማድረግ፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ማንኛ ውም ውሣኔ የሚተላለፈው በአደራ ጠባቂዎች ወይም በቦርዱ አባላት ሁለት ሦስተኛ ድምጽ ብቻ ነው፤

፫. በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚከናወኑ ተግባራት ተፈጻሚነት የሚኖራቸው በኤጀንሲው ሲጸድቅ ብቻ ነው፤

፬. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቶቹ በንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ)-(ሐ) የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እንዲፈጽሙ ውሳኔ መስጠት ይችላል።

## ክፍል ዘጠኝ
## ሕዝባዊ መዋጮ

### ፺፰. ለሕዝባዊ መዋጮ ስለማመልከት

፩. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሕዝባዊ መዋጮ ማካሄድ የሚችለው በኤጀንሲው ሲፈቀድለት ብቻ ነው።

፪. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚሰጥ ፈቃድ የሕዝባዊ መዋጮውን ዓላማ፣ የሚቆይበትን ጊዜ፣ ቦታውንና ሌሎች በኤጀንሲው የሚወሰኑትን መመዘኛዎች መያዝ አለበት።

፫. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገውን ተላልፎ የተሰበሰበው ማንኛውም ገንዘብ ወይም ንብረት በኤጀንሲው ተወርሶ ለተመሳሳይ የበጎ አድራጎት ወይም ማህበር

b. the rules of Charity should be modified by replacing all or any of the purposes of Charity with such other purposes, being in law charitable;

c. to amend the rules of charity regarding the procedures that has to be followed by officers to administer the charity.

2. Any action taken under Sub-article (1) of this Article must be passed by two-thirds of its trustees or board members.
3. The provisions of this Article shall apply only upon the prior approval of the Agency.
4. Notwithstanding Sub-article 1 of this Article the Agency may determine that the provisions of Sub-article 1 (a)-(c) be employed.

## SECTION NINE

## PUBLIC COLLECTIONS

### 98. *Application for Public Collection*

1. No Charity or Society may conduct any public collection unless permit is granted by the Agency.
2. The permit given under this Article shall specify the public collection purpose, duration, place and any other criteria set forth by the Agency.
3. Any money or property collected in contravention of Sub-article (1) of this Article shall be confiscated by the Agency and applied to the purpose of a similar

ዓላማ እንዲውል ይደረጋል፡፡

Charity or Society.

**፺፱. በማመልከቻ ላይ መወሰን**

፩. ሕዝባዊ መዋጮ ለመሰብሰብ ማመልከቻ ሲቀርብ ኤጀንሲው አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ ፈቃዱን በገደብ ወይም ያለገደብ መስጠት ወይም ውድቅ ማድረግ ይችላል፤

፪. ኤጀንሲው ማመልከቻውን ውድቅ ካደረገ ወይም በፈቃዱ ላይ ማናቸውንም ገደብ ሲያደርግ ለማመልከቻ አቅራቢው ውሣኔውን ከነምክንያቱ በጽሁፍ መስጠት አለበት፡፡

**99. *Decision on Application***

1. On receiving an application for public collections permit the Agency may make such inquires as it deems fit and determine whether to issue or refuse a permit with or without conditions.
2. Where the Agency refuses to issue a permit or attaches any condition to the permit, it must serve on the applicant written notice of its decision and the reasons for its decision.

**፻. የሕዝባዊ መዋጮ ፈቃድ የሚያስከለክሉ ምክንያቶች**

ኤጀንሲው በሚከተሉት ምክንያቶች የሕዝባዊ መዋጮ ፈቃድ ሊከለክል ይችላል፤

፩. ሕዝባዊ መዋጮው ለበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ለማህበሩ ዓላማ የሚውል ካልሆነ፤

፪. በአመልካቹ የቀረበው መረጃ ሐሰተኛ ወይም አሳሳች ከሆነ፤

፫. ሕዝባዊ መዋጮውን የሚያከናውኑት ሰዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸ የተደነገጉትን መመዘኛዎች የማያሟሉ ከሆነ፡፡

**100. *Grounds for Refusal of a Public Collections Permit***

The Agency may refuse to permit a public collection on the following grounds:

1. where the public collection is not going to be utilized for the purposes of the Charity or Society;
2. any information provided by the applicant is false or misleading;
3. where that any of the persons who are to conduct the public collection do not fulfill the requirements set forth in Article 70.

**፻፩. ሕዝባዊ መዋጮ የመሰብሰብ ፈቃድን ስለመሠረዝ**

፩. ኤጀንሲው በሚከተሉት ምክንያቶች ሕዝባዊ መዋጮ የመሰብሰብ ፈቃድን ሊሰርዝ ይችላል፤

ሀ. ፈቃዱ ከተሰጠ በኋላ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፰ ድንጋጌዎች እንዳልተሟሉ ሲረጋገጥ፤

ለ. ሕዝባዊ መዋጮው ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ እንዲተዳደር የተደረገ ሲሆን፤

ሐ. ፈቃዱ ሲሰጥ በኤጀንሲው የተጣለው ገደብ የተጣሰ ሲሆን፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ሕዝባዊ መዋጮ የመሰብሰብ ፈቃድ ሲሰረዝ የተሰበሰበው ገንዘብ ወይም ንብረት በኤጀንሲው ተወስዶ ለበጎ አድራጎት አላማ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**101. *Grounds for Revocation of a Public Collections Permit***

1. Agency may revock a public collection permit where:
   a. after a permission is granted, it is shown that the requiments under Article 98 have not been fulfilled;
   b. the public collection has been improperly administered;
   c. the conditions set by the Agency for granting the permit have not been complied with.
2. Where the Agency revoke a license under Sub-article (1) of this Article any money or property collected may be taken by the Agency and given to charitable purposes.

## ክፍል አሥር

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፻፪. ቅጣት**

፩. ማንኛውም የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የጣሰ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ይቀጣል፡፡

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም፤

ሀ. የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፸፯ በመጣስ የሂሳብ መዝገብ ያልያዘ፤ የተቀበለውን ገንዘብ፣ የገንዘቡን ምንጭና ወጭ ያልመዘገበ፤ የሂሳብ ሰነዶቹን የበጀት ዓመቱ ካበቃበት ቀን ጀምሮ ለአምስት ዓመታት ጠብቆ ያላቆየ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከብር ፳፻፻ (ሃያ ሺ ብር) በማያንስና ከብር ፶፻፻ (ሃምሳ ሺ ብር) በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

ለ. የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፸፰ በመጣስ ተቀባይነት ባላቸው ደረጃዎች መሰረት የተዘጋጀ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ ለኤጀንሲው ያልላከ ወይም ገቢው ከብር ፶፻፻ (ሃምሳ ሺ ብር) በታች ሲሆን ገቢን፣ ወጪንና ሃብትን ዝርዝር ለኤጀንሲው ያላቀረበ ወይም የሂሳብ መግለጫውንና ተያያዥ ሰነድ ለአምስት ዓመት ጠብቆ ያላቆየ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከብር (አስር ሺ ብር) በማያንስና ከብር ፳፻፻ (ሃያ ሺ ብር) በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

ሐ. የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፹፫ በመጣስ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን የባንክ ሂሳብ ከሚፈለገው ዝርዝር ጋር በየዓመቱ እና በተጠየቀ ጊዜ ለኤጀንሲው ያላቀረበ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከብር ፶፻፻ (ሃምሳ ሺ ብር) በማያንስና ከብር ፻፻፻ (መቶ ሺ ብር) በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

መ. የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፹፰ በመጣስ የየበጀት ዓመት አስተዳደራዊ ወጪውን ከበጀቱ ፴ በመቶ በላይ ያወጣ ወይም የዓላማ ማስፈጸሚያ ወጪውን ከ፸ በመቶ በታች ያደረገ የበጎ አድራጎት

## SECTION TEN

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**102.** ***Penalty***

1. Any person who violates the provisions of this proclamation shall be punishable in accordance with the provisions of the criminal code.

2. Notwithstanding subarticle (1) of this Article:

a. any Charity or Society whose in violation of article 77 fails to keep its books of accounts, to record money received, its source and the amount expended, to preserve any accounting records for at least five years from the end of its financial year shall be punishable with fine not less than birr 20,000.00 (Twenty thousand birr) and not exceeding Birr 50,000.00 (fifty thousand Birr) ;

b. any Charity or Society who in violation of article 78 fails to submit to the Agency an annual statements of account prepared in accordance with acceptable standards; to prepare the statements of receipts, payments and assests and send the same to the agency; to preserve any statements of accounts and related documents for atleast five years from the end of its financial year shall be punishable with fine not less than Birr 10,000.00 (ten thousand birr) and not exceeding birr 20,000.00 (twenty thousand Birr) ;

c. any Charity or Society who in violation of article 83 fails to report annually or upon request about all its bank accounts with the necessary particulars shall be punishable with fine not less than birr 50,000.00 (fifty thousand birr) and not exceeding Birr 100,000.00 (hundred thousand Birr) ;

d. any Charity or Society who in violation of article 88 fails to allocate not less than 70 percent of its expences in the budget year

ድርጅት ወይም ማህበር ከብር ፭፻ (አምስት ሺ. ብር) በማያንስና ከብር ፲፻ (አስር ሺ. ብር) በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተመለከተው ወንጀል ተሳታፊ የሆነ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ የተመለከተው የእስራት ቅጣት ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ ከብር ፲፻ (አሥር ሺህ ብር) በማያንስና ከብር ፳፻ (ሃያ ሺህ ብር) በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፻፫. <u>የገቢ ማስገኛ ስራዎች</u>

፩. የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከኤጀንሲው በጽሁፍ በሚሰጠው ፈቃድ መሠረት ለበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ አባላት ወይም ተጠቃሚዎች ሊከፋፈል የማይችል እና ገቢው ለዓላማው ማስፈጸሚያ የሚውል ከአላማው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ገቢ የማመንጨት ሥራዎች ሊያከናውን ይችላል፡፡

፪. ገቢ የሚያስገኙ ስራዎችን የሚሰራ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎቹን በተመለከተ የተለዩ የሂሣብ መዛግብት መያዝ አለበት፡፡

፫. የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ትርፉን ለአባላቱ አከፋፍሎ ወይም የተለየ የሂሣብ መዛግብት ሳይዝ ቢገኝ ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፪ መሰረት አግባብነት ያለውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

፬. በዚህ አዋጅ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በሌሎች ሕጎች ንግድን፣ ኢንቨስትመንትን እና ሌሎች ትርፍ ለማግኘት የሚሰሩ ሥራዎችን ምዝገባና ፈቃድ በሚመለከት የተደነገጉትን

for the implementation of its purposes and not exceeding 30 percent for its administrative activites shall be punishable with fine not less than Birr 5,000.00 (five thousand Birr) and not exceeding birr 10,000.00 (ten thousand Birr).

3. Any officer, or employee of a Charity or Society who participates in the criminal acts stated under Sub-article (2) of this Article shall, without prejudice to the applicability of the relevant provisions of the Criminal Code prescribing a penalty of imprisonment, be punishable with fine not less than Birr 10,000 (ten thousand birr) and not exceeding Birr 20,000 (twenty thousand birr).

**103.** ***Income Generating Activities***

1. Charities or Societies may, upon a written approval of the Agency, engage in income generating activities that are incidental to the achievement of their purposes and the proceeds of which shall not be distributed among the members or beneficiaries of the Charity or Society and are used to further the purposes for which the Charity or Society was established.

2. A Charity or a Society that undertakes income generating activities shall keep separate books of account with respect to such activities.

3. Where a Charity or Society is found to have distributed its profits or should it fail to keep separate books of account, the Agency shall take appropriate measures in accordance with Article 92 of this Proclamation.

4. Nothing in this Proclamation shall affect the requirements and procedures laid down in any other laws concerning the registration and licensing requirements for activities

መስፈርቶች እና ሥነሥርዓቶች አያስቀሩም፡፡

**፻፬. አቤቱታ እና ይግባኝ**

፩. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በኤጀንሲው አሰራር ላይ ተገቢውን የአስተዳደር እርከኖች ተከትሎ የሚቀርብለትን ማንኛ ውንም አቤቱታ ተቀብሎ በ ፲፭ ቀን ውስጥ መወሰን አለበት፡፡

፪. በማንኛውም ዋና ዳይሬክተሩ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ሰው ውሳኔው በተሰጠ በ፲፭ ቀን ውስጥ ለቦርዱ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡ ቦርዱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

፫. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ቢኖርም የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በቦርዱ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው ቦርዱ ውሳኔ በሰጠ ፲፭ ቀን ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ መሰረት በይግባኝ ሂደት ላይ የሚገኝ የምዝገባ ወይም የስረዛ ጉዳይ ከሆነ የሚመለከተው አካል የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ እንዳልተመዘገበ ወይም እንዳልተሰረዘ ይቆጠራል፡፡

**፻፭. ወንጀልን ስለመመርመርና ክስ ስለማቅረብ**

፩. በዚህ አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት በወጡ ደንቦች የተደነገገውን ማናቸውንም ወንጀል በተመለከተ የሚካሄድ የምርመራ ወይም የክስ ማቅረብ ሂደት በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ይመራል፡፡

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም ኤጀንሲው ለወንጀል ክስ የሚረዱ ማናቸውንም ማስረጃ በማደራጀት ክስ የመመስረት ሥልጣን ላለው አካል የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

related to trade, investment or any profit making activities.

**104.** ***Claims and Appeals***

1. The Director General of the Agency shall decide over claims that have exhausted administrative stages and made to him in relation to the Agency's activities within 15 days.
2. Any person aggrieved by any decision of the Director General may appeal to the Board within fifteen days from the date of the decision. The decision of the Board shall be final.
3. Notwithstanding Sub-article (2) of this Article, Ethiopian Charity or Society aggrieved by the decision of the Board may appeal to the Federal High Court within 15 days from the date of the decision.
4. Any Charity or Society in the process appeal, where it is in relation to registration or cancellation shall be deemed not registered or cancelled until final decision is rendered by the concerned authority.

**105.** ***Investigation and Prosecution of Offences***

1. Investigations and prosecution in respect of any offence under this Proclamation or any regulations made hereunder shall be conducted by organs authorized in accordance with the Criminal Procedure Code.
2. Notwithstanding Sub-article (1) of this Article, the Agency shall collect and organize any evidence necessary for criminal prosecution and submit the same to the appropriate authority.

**፻፮. መዋሐድ**

፩. ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት አግባብነት ባላቸው ህጐችና በመተዳደሪያ ደንባቸው መሠረት በአዲስ ስም ወይም ከሚዋሃዱት በአንዱ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ስም ሊዋሐዱ ይችላሉ፡፡ ውህደቱ ሲፈጸም የቀድሞ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት መብትና ግዴታ ወደ ተዋሃደው ድርጅት ይተላለፋል፡፡

፪. የተዋሃደው አዲስ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በዚህ አዋጅ መሠረት መመዝገብ አለበት፡፡

**፻፯. መከፋፈል**

፩. የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር መተዳደርያ ደንቡ የሚፈቅድ ከሆነ እና አግባብነት ያለው አካል ከፈቀደ በሕግ መሰረት ሊከፋፈል ይችላል፡፡

፪. የተከፋፈለው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ስልጣን ያለው አካል ተቃራኒ ውሳኔ እስካልሰጠ ድረስ የተከፈለው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የቀድሞ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ላለበት ግዴታና መብት እኩል ተካፋይ ነው፡፡

፫. የቀድሞው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሕልውና የሚያበቃው ለአዲሶቹ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት የምዝገባና ፈቃድ የምስክር ወረቀት ሲሰጥና የንብረት ክፍፍል ሲደረግ ነው፡፡

፬. በሁሉም አዲሶቹ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ስምምነት ከነሱ አንዱ የቀድሞውን የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ስም ይዞ እንዲቆይ ኤጀንሲው ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**106. *Merger***

1. Two or more Charities or Societies may merge into one under a new name or under the name of one of the former Charity or Society in accordance with relevant laws and in accordance with their rules. The rights and obligations of the former Charities or Societies shall be transferred to the newly formed organization.
2. The newly established Charity or Society shall be registered anew in accordance with this proclamation.

**107. *Division***

1. A Charity or Society may be divided into two or more organizations where its rules allow and its competent organ so determines.
2. Unless determined otherwise by the competent organ of the original Charity or Society the Charities or Societies that result from the division shall bear the obligations and utilize the rights jointly.
3. The existence of the former Charity or Society shall cease at the time when the certificates of license and registration are issued to the new Charities or Societies and division of property is completed.
4. The Agency may allow one of the new Charities or Societies to retain the name of the previous Charity or Society where the retention of such name is agreed upon by all the new Charities or Societies.

**፻፰. ስለ መቀየር/መለወጥ**

፩. ማንኛውም የበጐ አድራጐት ድርጅት በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት በድርጅቱ የበላይ አካል ውሣኔ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፪)፣ (፫) ወይም (፬) ከተጠቀሱት የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ወደ አንዱ ሊቀየርና በኤጀንሲው ሊመዘገብ ይችላል፡፡

፪. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት በዚህ አዋጅ እና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ዓይነት ወደ አንዱ ሊቀየርና በኤጀንሲው ሊመዘገብ ይችላል፡፡

**108. *Conversion***

1. Any Charity may be converted into any of the types of charities listed under sub articles (2), (3) and (4) of Article 2 of this proclamation and be registered with the Agency where its competent organ so decides in accordance with its rules.
2. Any Charity may be converted into one of the forms of charities under this proclamation and be registered with the Agency where its competent organ so decides in accordance with its rules.

**፻፱. ደንብ የማውጣት ሥልጣን**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**109. *Power to Enact Regulations***

The Council of Ministers may enact regulations necessary to give effect to this Proclamation.

**፻፲. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**110. *Inapplicable Laws***

Any law, regulation, directive and customary practice contrary to this Proclamation shall have no effect.

**፻፲፩. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

፩. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ቀድሞ በነበረው ሕግ የተገኘ መብትና ግዴታ ይህን አዋጅ እስካልተቃረነ ድረስ ይቀጥላል፡፡

፪. ቀደም ሲል የተመዘገቡ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደገና መመዝገብ አለባቸው፡፡

**111. *Transitional Provisions***

1. Any right or duty arising under any provision of the repealed laws shall continue unless it contravenes this Proclamation.
2. All Charities and Societies previously registered shall re-register within one year of the coming into effect of this Proclamation.

**፻፲፪. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ከታተመበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ____ወር፤____ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

ግርማ ወ/ጊዮርስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት

**112.** ***Effective Date***

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazzeta.

Done at Addis Ababa, this __th day of __, 2009.

GIRMA WOLDEGIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA